# ትንሣኤ



ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ለድንግል ማርያምና በከበረ [illegible]
ክርስቶስ መስቀል እንሰግዳለን።



[illegible] በሕልም እንደነገረው ሕጻኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብፅ ሲሰደድ፡-

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 49 ጥቅምት ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር ፲፩6616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

## ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| የሥነ ጽጌያት ውበት | ፪ |
| የቅዱስ ማቴዎስ ከቀራጭነት ወደ ወንጌላዊነት መጠራት | ፫ |
| ከዲቁና እስከ ዲግሪ | ፬ |
| መምህር ሠረገላ፡ | ፯ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘይና የንግግር ጥበብ | ፰ |
| የጉጂ ብሔረሰብእ ባህል | ፱ |
| ምን እንርዳዎ | ፲ |
| ብቻህን አትሂድ | ፲፫ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲፬ |
| ክርስቲያን በተስፋ | ፲፯ |
| ወደ ምድረ ግብጽ መሰደድ | ፲፱ |
| የቤተ ሰብእ ዐምድ | ፳ |
| ይህን ያውቁ ኖርዋል? | ፳፩ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በአሁኑ ጊዜ በየቦታው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እየተተከሉ ናቸው ነገር ግን ቀደም ብለው የተተከሉት መገልገያና አገልጋይ በማጣት በችግር ላይ ይገኛሉ በዕለተ እሑድ እንኳ ሥርዐተ ጸሎት አይፈጸምባቸውም ስለዚህ ሁኔታ ምን ትላላችሁ?

ሊቀ ዲያቆናት ታደሰ ዐለሙ
ከገነተ ጽጌ ቅ ጊዮርጊስ
አዲስ አበባ

ሊቀ ዲያቆናት ታደሰ ዓለሙ ጥያቄዎን ተመልክተነዋል በጊዜያችን የአብያተ ክርስቲያናት መተከል ለክርስቲያኖች መንፈሳዊ ደስታ ነው ፣ አገልጋይ በማጣት ችግር አለ ያሉትም ችግሩ ከአሠራር ጉድለት ነው እንጂ በኢትዮጵያ የካህናት እጥረት አለ ለማለት አይቻልም ፣ ምክንያቱም የካህናቱ ብዛት ሁለት መቶ ሽህ ያህል ሲሆን የአብያተ ክርስቲያናቱም ቁጥር ሃያ ሽህ ያህል ነው ስለሆነም ለእያንዳንድዋ ቤተ መቅደስ አሥር ፣ አሥር ካህናት ይደርሳሉ ማለት ነው ፣ በከተማ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ከሃምሳ እስከ መቶ የሚሆኑ ካህናት ይገኛሉ በገጠር ግን አንድም የለም ከተባለም ችግሩ ከአሠራር ጉድለት ይሆናል የተባለው ይኸው ነውና ካህናት ከበዙበት ወደ አነሱበት ሄደው እንዲያገለግሉ ማድረግ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ አዲስ ስለሚተከሉትም አብያተ ክርስቲያናት ምእመናኑ ለአገልጋዮቹ ደመወዝና የመገልገያውንም ንዋየ ቅድሳት ለማቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን አረጋግጠው ለክፍሉ ጳጳስ አመልክተው በጳጳስ ተፈቅዶ ስለሚተከል ችግሩን የሰበካው ምእመናን እያስወገዱና ጉድለቱንም እያሟሉ ስለሆነ የሚያስደስት እንጂ የሚያጠያይቅ አይደለም ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በጥምቀት በእመቤታችን በድንግል ማርያም በጻድቃን ፣ በሰማዕታትና በቅዱሳን መላእክት በዓል ታቦት ወጥቶ ዑደት ከተደረገ በኋላ ወደ መንበሩ በሚመለስበት ጊዜ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን በግ ወይም ሰንጋ ታርዶ ታቦቱን የተሸከመው ካህን ደሙን ረግጦ ሲገባ አይቻለሁ ይህ ነገር የደስታ ምልክት ነው ወይስ የልማድ? ትንሣኤ ምን አስተያየት አለው?

የመጽሔቱ ተከታታይ
መኰንን ተረፈ
ከሰበታ

አቶ መኰንን ተረፈ ስለጥያቄዎ እናመሰግንዎታለን ። ታቦት ወጥቶ በሚገባበት ጊዜ በግ ወይም ሰንጋ መታረዱ በእውነት አረታዊ ልማድ እንጂ የሐዲስ ኪዳን ሥርዐት አይደለም ።

በዳዊት ዘመን የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ገብቶ በተዘጋጀለት ድንኳን ባረፈ ጊዜ ሠንጋ ታርዶ ሥጋው ለሕዝብ ታድሎአል (2ሳሙ.6፡ 16-19 ነገር ግን ጠያቂው እንዳዩት በግ ታርዶ ታቦቱን የተሸከመው ካህን ደሙን እንዲረግጠው መደረጉ ፍጹም ስህተት ነው ። ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ድርጊት አትቀበልም ። እንዲደረግም አታስተምርም ። ደም ረግጦ ወደ ቤተ መቅደስ የገባው ካህንም ከመሐይምናን ያልተሻለ ይሆናል እንጂ መቃወም በተገባው ነበር ። ምእመናኑ ቤተ ክርስቲያን ተሳላሚዎችንና ካህናቱን ለመጋበዝ ከፈለጉ ግን ለስለት ያቀረቡትን የሥጋ ከብት ማዘጋጃ ቤት በሚፈቅደው አካባቢ አርደው ሥጋውን መጋበዝ ይችላሉ ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በአክሱም የምትገኘው ጽላት በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከኢየሩሳሌም ወደ ሀገራችን እንደመጣች የታሪክ መጻሕፍት ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ ይህችው ጽላት ለሙሴ የተሰጠችው ናት? ወይስ በዚያች አይነት የተዘጋጀች ሌላ ናት?

የሃምሳ አለቃ ታፈሰ ተስፋዬ
የመ.ሣ.ቁ. 1747
አዲስ አበባ

የ፶ አለቃ ታፈሰ ተስፋዬ መጽሔታችንን በመከታተል ይህን ጥያቄ ስላቀረቡልን እናመሰግናለን ። እርግጥ ርስዎ እንዳሉት የሙሴ ጽላት ወደ ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ እንደመጣች የውጭ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ታሪክ ይናገራል እንግዲህ ጽላትዋ በሰሎሞን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣች ሲተረክ በሌላ በኩል ደግሞ ከሰሎሞን በኋላ በኢየሩሳሌም እንደነበረች ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል 1. ዜና መዋዕል 35.3 ከሰሎሞን እስከ ኢዮስያስ 300 ዘመን ነው ። ከዚያም በኋላ በኤርምያስ ዘመን በዚያው በኢየሩሳሌም እንደነበረችና በባቢሎን ምርኮ ጊዜ እንደጠፋች የአይሁድ ባለታሪኮች ይናገራሉ ነገር ግን ለሙሴ የተሰጡት ሁለት ጽላት ነበሩ ። ''ጽላት'' የሚለው ቃልም በግእዝ ብዛትን እንጂ ነጠላን አያመለክትም ። በነጠላ ጽሌ ነው ። ስለዚህ ወደ ሀገራችን የመጣችው ከሁለቱ ጽላት አንድዋ ጽሌ ናት ።

ሆኖም የመጀመሪያዎች ከእግዚአብሔር ለሙሴ የተሰጡት ጽላት ወዲያው ሙሴ ከደብረ ሲና እንደወረደ መስበራቸውንና ሙሴ በተሰበሩት ምትክ ሌሎችን ሁለት እንደቀረፀና ቃላቱም በግብር አምላካዊ እንደተጻፉለት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል እንግዲህ ወደ ሀገራችን የመጣችው ጽሌ እስከ ኢዮስያስም በኢየሩሳሌም የነበረችው ጽሌ ሙሴ በመጀመሪያዎቹ አስመስሎ እንዲቀርፅ በታዘዘው መሠረት የቀረፃቸው ናቸው።

ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርዕሰ አንቀጽ

# የሥነ ጽጌያት ውበት

ልዑል እግዚአብሔር ከዕለተ እሁድ ጀምሮ እስከ ዕለተ ዓርብ በስድስት ቀናት የፈጠራቸው ፍጥረታት ሃያ ሁለት መሆናቸውን የሥነ ፍጥረታት ሊቃውንት ይናገራሉ ፤ ከሃያ ሁለት ፍጥረታት መካከል ሁለቱ ሰውና መላእክት የእግዚአብሔርን ስሙን ለመቀደስና ክብሩን ለመውረስ የተፈጠሩ ናቸው ። የቀሩት ፍጥረታት ግን ለአንክሮ ፡ ለተዘክሮ ብቻ የተፈጠሩ መሆናቸው ይነገራል ፤ ለአንክሮና ለተዘክሮ ከተፈጠሩትም ፍጥረታት መካከል አንደኛውን ክፍል የያዙት ዕፅዋት ናቸው እነርሱም የተፈጠሩት በዕለተ ሠሉስ (በሦስተኛው ቀን) ሲሆን በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ተመድበው ይነገራሉ ።

አንደኛ በምሳር የሚቆረጡ ታላላቅ ዛፎች ፣ ሁለተኛ በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት ፣ ሦስተኛ በእጅ የሚለቀሙ አትክልት ናቸው ፤ ከዕፅዋት መካከል አብዛኞቹ ፍሬ ከመስጠታቸው በፊት አበባ የማውጣት ባሕርይ አላቸው ያለ አበባ የሚያፈሩ ዕፅዋት በጣም አንስተኞች ናቸው ።

ስለ ዕፀዋት አፈጣጠር ቅዱስ መጽሐፍ ሲገልጽ "እግዚአብሔርም ምድርን ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድር ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ ፤ እንዲሁም ሆነ ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደወገኑ ፣ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደወገኑ አበቀለች እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ" ይላል ። ዘፍ 1. 11 - 12

እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች እያፈራረቀ ከሚያቀርብላቸው አራት ክፍላተ ዘመን አንደኛው ዘመነ መፀው የሚባለው ነው ፤ ይህም ከመስከረም ፳፮ ቀን እስከ ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ያለው ዘመን ነው በዚህ ዘመን የሰው ልጅ የሥነ ጽጌያትን ውበት ፣ የመሬትን በልምላሜና በፍሬ መሸፈን ፤ የውሃዎችን መጥራት ፣ የሰማይን በከዋክብት መሸለም በዓይኖቹ አተኩሮ እየተመለከተ ሠሪያቸውን እግዚአብሔርን እጅግ በጣም የሚያደንቅበት ነው ።

ጠቢቡ ሰሎሞን በዘመነ መጸው ስለሚታየው የሥነፍጥረት ውበት ሲገልጽ "እነሆ ክረምት አለፈ ዝናቡም አልፎ ሄደ አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ የዜማም ጊዜ ደረሰ (የሽመላ) የአሞራም ቃል በምድራችን ተሰማ በለሱ ጐመራ ወይኖችም አበቡ መዓዛቸውንም ሰጡ" ብሏል ። መሐልየ ሰሎሞን 2.11 - 13

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ሲያስተምርበት በነበረው ወቅት በዘመናቸው አምረውና አሸብርቀው የሚታዩትን አበቦችን ምሳሌዎች በማድረግ ሲያስተምር " የምድረ በዳ አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ ፤ እነርሱም አይደክሙም ፣ አይፈትሉም ፤ ነገር ግን እላችኋለሁ ሰሎሞን እንኳን በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰር" ብሏል ማቴ 6.28 ክርስቶስ ይህንን የተናገረው የአበቦች የተፈጥሮ ውበት በምድር ላይ ከሚበቅሉት ዕፀዋት ሁሉ ብልጫ ያለው መሆኑን ለሰው ልጆች ለማስረዳት ሲል ነው

በዚህ ዓለም ሀብተ ሥጋ ከተሰጣቸው መሪዎች ሁሉ ከሰሎሞን የሚስተካከል አለመኖሩ ይነገራል ጠቢቡ ሰሎሞን ከብልጽግናው ብዛት የተነሣ ወርቁንና ብሩን እንደ ሀረግ እየሳበ እንደ አበባ እያፈነዳ በልብሱና በዕቃው እንዲሁም በሕንፃዎች ላይ ለጌጥ ይጠቀምበት ነበር ፤ ነገር ግን እርሱ ለሚያደርገው ጌጣጌጥ ሁሉ አብነት አድርጐ የተነሣው አበቦችን ሲሆን የአበቦች ውበት ግን የባሕርያቸው ነው ስለዚህ የአበቦች ውበት በምድር ላይ ከሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ ተመሳሳይ ሊገኝለት አይችልም ።

ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በባሕርዩ የማይታወቅ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይታወቃል ተብሎ እንደተጻፈው የሰው ልጆች የሥነ ጽጌያትን ውበትና የሌሎችንም ፍጥረታት ሁኔታ አተኩረው እየተመለከቱ የሚያደንቁት ሠሪያቸውን እግዚአብሔርን ነው ።

የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በዘመነ መጸው የሥነ ጽጌያትን የተፈጥሮ ውበት የከዋክብትን ድምቀት የውሀዎችን ጥራት የምድርን ፍሬያት እየተመለከተ የእግዚአብሔርን ከሃሊነትና ጠቢብነት ሲገልጽ በአርያም የሚኖር እግዚአብሔር ኪነ ጥበቡ ዕፁብ ድንቅ ነው ሰማይን በከዋክብት የጋረደ ምድርን በአበቦች ያሸበረቀ እርሱ ነው በማለት ዘምሯል ።

ስለዚህ ሰውየሥነ ጽጌያትን ውበት እየተመለከተ "አቤቱ ሥራህ ዕፁብ ድንቅ ነው ፣ ሁሉንም በጥበብ አደረግህ እያለ ዘወትር እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባዋል ።



# የቅዱስ ማቴዎስ ከቀራጭነት ወደ ወንጌላዊነት መጠራት

ማቴዎስ ማለት ሀብተ አምላክ ወይም የአምላክ ስጦታ ማለት ነው ። ይህም በዕብራይስጥና በአራማይክ ቋንቋ ነው ።

እንደ ቅዱስ ማርቆስ አጻጻፍ ማቴዎስ የእልፍዮስ ልጅ ሌዊ ይባላል ። በዚህም መሠረት የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ወንድሙ እንደሆነ የገመቱ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት አሉ ። ሉቃስ ግን በቀላሉ ሌዊ በማለት ብቻ ይጠራዋል ።

ይሁን እንጂ በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የስም ዝርዝር ውስጥ በ2ኛውና በ3ኛው ወንጌል በተራ ቁጥር 7ኛ ሲሆን ስሙም ማቴዎስ በመባል ተጠቅሶአል በመጀመሪያው ወንጌልና በግብረ ሐዋርያት ደግሞ በተራ ቁጥር 8ኛ ሆኖ ማቴዎስ በመባል ተመዝግቦአል ። ማር. 3 16-19 ማቴ 10፡ 2-4 ። ሉቃ 6፡14 - 16 የሐዋ. 1 ፡ 13

"እንግዲህ ሌዊ ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት የተጠራበት ስሙ ሲሆን ማቴዎስ ደግሞ ከተጠራ በኋላ የተጠራበት ስሙ እንደሆነ በስምዖን ጴጥሮስ አንጻር መገመት ይቻላል ። ከዚህም ሌላ በአይሁድ ዘንድ ለአንድ ሰው ሁለት ስሞች ሊኖሩት ስለሚችል ፡ ማቴዎስ ቅድመ ተጸውኦ በሁለት ስሞች ሊጠራ ይችላል ። ማር.1 ፡ 14 ። ማቴ.9፡9 ። ሉቃ. 5፡27-28 ።

ማቴዎስ ቅድመተጸውኦ (መጠራት) ቀራጭ ነበረ ። በቀራጭነቱም በአይሁድ ኅብረተሰብ ዘንድ እጅግ የተጠላና የተናቀ ሰው ነበር ። ቀረጥ የመሰብሰብ ሥራ ዛሬ በሰለጠነው ዓለም እንደሚሠራው የቀረጥ አሠራር አልነበረም ። ግን ቀራጩ እንደፈቀደ ብቻ ይሠራ ነበር ።

ለምሳሌ ቀራጩ ማንኛውንም ሰው በየትም ቦታ ለማቆምና እቃውን ለመበርበር የሚነዳውን ከብት ለማገድ የጫነውን እህል በመዘርገፍ ልብሱንም አስወልቆ ለመፈተሽ ወዘተ ሥልጣን ነበረው ግን ባል ባገባች ሴት ላይ ይህን ሁሉ ማድረግ እንደማይችል የሥልጣን ገደብ ነበር ። ከዚህም ጋር አንድ ግለሰብ አንድ የሚሸጥ ነገር ከቤቱ ይዞ ይወጣል ከዚያም ለዋና መንገድ ወይም ለድልድይ በገበያ ውስጥ ለመደብር የያዘውንም ከሸጠ በኋላ የገቢ ቀረጥ በጠቅላላ በአንድ ዕቃ ወይም ከብት ከአራት ጊዜ በላይ ይከፍላል ። በእነዚህም ቦታዎች ሁሉ ቀራጮች ተመድበው ይቆማሉ ። ይህም የቀረጥ ክፍያ በወንዶች ከ12 እስከ 65 በሴቶች ከ12-55 ዕድሜ ባላቸው ላይ የጸና ነበር ። ከዚህም የተነሣ ቀራጮች ሁሉ እጅግ የተጠሉና የተናቁ ነበሩ ።

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ቀራጮች እንደ አመንዝሮች ፡ ዓመፀኞችና ሌቦች ይቆጠሩ ነበር ሉቃ 18፡11-12 በዚህ አንጻር ማቴዎስ ቀራጭ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች የሚጠሉት ሰው ነበር ።

የማቴዎስ የግብር መቀበያ ቦታ በቅፍርናሆም ውስጥ ከገሊላ ባሕር ወደብ አጠገብ ባለው ዋና መንገድ ነበር ። አንድ ቀንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ በኩል ሲያልፍ ማቴዎስን በመቅረጫው ቦታ ተቀምጦ አገኘውና "ተከተለኝ" በማለት ጠራው ። ማቴዎስም ሁሉን ትቶ ግን ቀረጥ ሲቀበል ይጽፍበት የነበረውን ብርዑንና ቀለሙን ሳይተው ጌታን ተከተለ ። በቤቱም ጌታችንን ለምሳ ጋበዘው በግብዣውም ላይ የማቴዎስ ጓደኞች ቀራጮች ተገኝተው ነበር ።

ነገር ግን ፈሪሳውያን ጌታ በማቴዎስ ቤት በመጋበዙ አጉረምርመዋል ። ምክንያቱም ቀራጩ ማቴዎስ እንደ ኃጢአተኛ ይቆጠር ስለነበር ነው ።

ይሁን እንጂ ጌታችን "ሐኪሙን የሚፈልጉት በሽተኞች እንጂ ጤናማዎች አይደሉም እንደዚሁም ሁሉ እኔ ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም" በማለት መልሶላቸዋል ።

በዚህ ቃል መሠረት በኅብረተሰቡ ዘንድ የተጠላው ማቴዎስ ተወደደ ኃጢአተኛው ጸደቀ ለራሱ ጥቅም ሲል ሰዎችን ያስጨንቅ የነበረው ስለ ሰዎች ደኅንነት ይጨነቅ ጀመረ ። ባጠቃላይ አነጋገር ቀራጩ ሐዋርያና ወንጌላዊ ሆነ መደቡ ከአመንዝሮችና ከዓመፀኞች ጋር የነበረው ከአሥራ ሁለቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ ።

ቅዱስ ማቴዎስ ከአራቱ ወንጌሎች የመጀመሪያውን ወንጌል ጻሐፊ እንደሆነ ትውፊት ያስረዳል የጻፈበትም ቋንቋ ዕብራይስጥ ሲሆን ሀገሩ ይሁዳ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይናገራል ኤውሴብዮስ የቤ ክ ታሪክ 3.38.6፡5፡10 .3 ። ስለዚህም የመጀመሪያዎቹ የክርስትና እምነት አባቶች "ማቴዎስ እንደ ጻፈው" የሚል ርእስ ሰጥተውታል ።

ትውፊት እንደሚያስረዳ ማቴዎስ በመጀመሪያ ለሀገሩ ለይሁዳ ሰዎች ወንጌልን አስተምሮአል ኤውሴብዮስ የቤ. ክ ታሪክ 3፡24፡5 ቀጥሎም በኢትዮጵያ እንዳስተማረ ሶቅራጥስና ሩፊኖስ ተረክዋል ሩፊኖስ . 1.19 አምብሮስ ደግሞ ማቴዎስ በፔርሲያ እንዳስተማረ ጽፎአል ።

ቅዱስ ማቴዎስ ለሐዋርያነት ከተጠራ በኋላ አንድ ቀን እንኳን ሥጋ እንዳልበላ ግን ቅጠላቅጠል ብቻ የሚመገብ ሐዋርያ እንደነበረ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ያስረዳል ቀሌ. 2.1

ማቴዎስ በክርስቲያኖች የምልክት ጥበብ (ሲምቦል) ክንፍ ያለው የሰው ምልክት ገጸ ሰብእ ተሰጥቶታል ። በክርስቲያን የሥዕል ጥበብ ዓለም ደግሞ በቀኝ እጁ ሰይፍ በግራ እጁ የገንዘብ ከረጢት እንደያዘ ይሣላል ። ይህም ቅድመ ተጸውኦ ቀራጭ እንደነበረና በኋላም ስለክርስቶስ ሰማዕት እንደ ሆነ ያመለክታል ።

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ

## ከዲቁና እስከዲግሪ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለብዙዎች ኢትዮጵያውያን የትምህርት እናት እንደመሆኗ መጠን ብዙዎችን በትምህርት ኮትኩታ በማሳደግ ለዘመናዊ ሥልጣኔ መሠረትና መሸጋገሪያ ሆና የቆየች ናት ። ስለዚህም የትምህርት ጮራ ባልፈነጠቀበትና እንደ አሁንም ባልተስፋፋበት በዚያ ጨለማ ዘመን ወጣቶች መሠረታዊ ትምርታቸውን ተምረው እንዲያነቡ ፤ እንዲጽፉ ፤ ቅኔ እንዲቀኙ ፤ እንዲዘምሩ ፤ በምስጢር እንዲራቀቁና ደራስያን ሁነው መጽሐፍ እንዲጽፉ ድርሰት እንዲደርሱ በማድረግ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ግንባር ቀደም ሆና የበኩሉዋን ድርሻ ስትወጣና የማይናቅ አገልግሎት ስታበረክት ኖራለች አሁንም በማበርከት ላይ ትገኛለች ።

ብዙ ወጣቶች ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት የሚተዳደሩት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ርዳታ ነው ። በዚህ ሁኔታ ነበር አባቶቻችን ሊቃውንት ተምረው ያደጉትና ራሳቸው ለቁም ነገር በቅተው ዕውቀታቸውን በነፃ እያስተማሩ ወገናቸውን በመርዳት አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን በሙሉ ስሜት ሲያገለግሉ የኖሩት ።

ዘመናዊ ትምህርት በተጀመረበት ወቅት በመማርም ሆነ በማስተማር ግምባር ቀደም ሆነው የተገኙት የቤተ ክርስቲያን ምሁራን የሆኑ ወጣቶች እንደነበሩ ይነገራል ። የቤተ ክርስቲያን ምሁራን የሆኑ ወጣቶች ያለመሰልቸት ለማጥናት በቂ ልምድና ችሎታ ስላላቸው በፈተና አይወድቁም ስለሆነም ትምህርታቸውን ከግቡ በማድረስ በድግሪና በድፕሎማ ከመመረቅ አልፈው ለዶክተርነት ማዕረግ የበቁ ብዙዎች ናቸው ። በዚህ ዓመት በከፍተኛ ማዕረግ የተመረቁ ብዙዎች ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ትምህርታቸውን ፈጽመው በድግሪ ከተመረቁት መካከል ፤

1ኛ ዲያቆን ቀለመወርቅ ሉልዬን
2ኛ ዲያቆን መንክር ቢተውን
3ኛ ዲ . ወልደ ሥላሴ ይትባረክን

አነጋግረናቸዋል ። እነዚህ ሦስት ወጣቶች ጥንታዊ ብሔራዊና መንፈሳዊ ትምህርታቸውን የሚቻላቸውን ያህል ከተማሩ በኋላ ዘመናዊውን ትምህርት ጀምረው በድግሪ እስከተመረቁበት ጊዜ ድረስ በትርፍ ጊዜያቸው ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ቤተ ክርስቲያንም እነሱን እየረዳቻቸው የተማሩ ናቸው። ስለሆነም እነሱ የሰጡትን አስተያየት ለዚህ ጽሑፍ መነሻ በማድረግ በዚህ እትም አቅርበነዋል ።



ዲያቆን ቀለመ ወርቅ ሉልዬ

### ዲያቆን ቀለመወርቅ ሉልዬ

ቀለመ ወርቅ መሠረታዊ የንባብ ትምህርቱን አጠናቆ ዳዊት ከደገመ በኋላ ቅዳሴ ፤ ቅኔና ዜማ ተምሮ በዚሁ ዕውቀቱ ቤተ/ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ሳለ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በመንበረ ፀባዖት ቅ . ሥላሴ ካቴድራል በዲቁና ሥራ ተቀጥሮ በዚሁ ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ ካቴድራሉ ለዲያቆናትና ለቀሳውስት ባቋቋመው ት/ቤት የ1ኛ ና መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በዚያው እንዳለ በዳግማዊ ምኒልክ ት ቤት የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠቃሏል።ከዚያም በአ.አ. ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ትምህርቱን እየተከታተለ ቆይቶ በድግሪ ለመመረቅ መብቃቱን ገልጧል ።

በዚሁ ዘመን ውስጥ በልብስ በቀለብ በመጠለያና በመሳሰለው ሁሉ እንደ እናትና አባት ሆና የረዳችው ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ዲያቆን ቀለመወርቅ አመልክቶ እሱም በዲቆና ብቻ ሳይሆን በመዘምርነት ፤ በሰንበት ት ቤት በመምህርነትና ለመምህራኑም ማኅበር ሊቀ መንበር በመሆን ከማገልገሉም ብላይ አብዮቱ ከፈነዳ ወዲህ ካህናት በልማት እንቅስቃሴ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና መንፈሳዊ ተሐድሶም እንዲኖራቸው በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አብያተ ክርስቲያናት የስብከተ ወንጌል ማኅበር እየተባለ ሲጠራ በነበረው በምክትል ሊቀ መንበርነትና በዋና ጸሐፊነት በሚሠራበት ወቅት በየቤተ ክርስቲያኑ እየተዘዋወረ ያልተቆጠበ አገልግሎት ማበርከቱን ጠቁሟል።

ዲያቆን ቀለመወርቅ በሰበካ ጉባኤ በኩልም ስለሰጠው አገልግሎት ሲገልጥ « በክረምት ወራት በሚደረገው የልዑካን ሥምሪት አንዱ በመሆን በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት በመዘዋወር የበኩሌን አስተዋጽኦ አድርጌያለሁ » ብሏል እንዲሁም ቀደም ሲል በተደረገው የእናት አገር ጥሪ መልሶ ማቋቋም የነበረው የካህናት ማህበር ከ23 000 ብር የማያንስ ገቢ ሲያደርግ ለዚህ ዝግጅት ግምባር ቀደም ሆኖ በማስተባበር የሠራ ሲሆን አሁንም የስዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ዳቦ ቤትና ንዋየ ቅድሳት ማዘጋጃ ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅና ሂሳብ ሹም ሆኖ በማገልገል ላይ እያለ በ1973ዓ.ም.የትምህርት ዘመን በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ በቢ . ኤ ድግሪ ተመርቋል ።

ወጣት ቀለመ ወርቅ ወደፊት ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ስላለው ዕቅድ ሲያብራራ « ከደጀ ሰላም እስከ ዩንቨርስቲ ፤ ከዲቁና እስከ ድግሪ ያደረሰችኝና በትምህርት ወልዳ ያሳደገችኝን እናት ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ሙሉ ፈቃድ ስላለኝና የክርስትና እምነቱም ስለሚያስገድደኝ የሥራ ቦታና የሚሠራ ሥራ እንዲሁም ተቀባይ ካለ ዓቅሜ በሚፈቅደው መጠን ሁሉ እስከ መጨረሻው ድረስ ለማገልገል እችላለሁ ሲል ቃል ገብቶ ምናልባትም በሌላ መሥሪያ ቤት በሥራ ቢመደብ እንኳን በሰበካ ጉባኤ አባልነት ፤ በቅዳሴ ፤ በመዘምርነትና በመሳሰለው ሁሉ በትርፍ ጊዜው በነፃ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆኑን ገልጦአል ።

በመጨረሻም በሰጠው አስተያየት «በየትም ቦታ ብሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን መንፈሳውያን ወጣቶች ባለኝ ችሎታና ዓቅም በሃይማኖት ትምህርት ከመርዳት ወደ ኋላ አልልም » በማለት አስረድቶ በተጨማሪም በየትኛውም በሚኖርበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤን ለማቋቋምና ለማጠናከር ዕቅድ እንዳለው አረጋግጧል ።



ዲያቆን መንክር ቢተው

ይህ ወጣት በመንፈሳዊ ትምህርት የሠለጠነ ከመሆኑ የተነሣ ቀደም ሲል ንባብና ዳዊት ካወቀ በኋላ ቅኔና ዜማ የተማረ ሲሆን በ1961 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በዲቁናና በመዘምርነት እያገለገለ ዘመናዊ ትምህርቱን ተከታትሎ ለከፍተኛ ደረጃ በመብቃቱ በአጠቃላይ የኅብረተሰብ ሳይንስ (አፕላይድ ሶሲኦሎጂ) በቢ..ኤ.ድግሪ ተመርቆ በባህል ሚኒስቴር ውስጥ ተመድቦ በመሥራት ላይ ነው ።

ለወደፊቱ ቤተ ክርስቲያንን በምን ሁኔታ ልታገለግላት ፈቃደኛ ነህ? ለሚለው ጥያቄ ዲያቆን መንክር ሲመልስ « እንደኔ አስተያየት በሁለት ዓይነት መንገድ አገልግሎት መስጠት ይቻላል ይህም 1 የግል አገልግሎት ሲሆን 2ኛው ደግሞ ድርጅታዊ አገልግሎት ነው የግል የሚባለው እንደኔ አስተያየት ክርስቲያናዊ ግዴታን ለመወጣት በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ራስን መድቦ ችሎታ በሚፈቅደው መሠረት ያለ ምንም ጥቅም በራስ ፈቃድና መንፈሳዊ ስሜት ነፃ የሆነ የግል አገልግሎት ማበርከት ነው ። በዚህ መሠረት በሰንበት ቀንና በዓመት በዓላት ቅዳሴ በመቀደስ ፤ ማኅሌት በመቆምና በሌላም አገልግሎት በመሰለፍ በትርፍ ጊዜዬ ነፃ አገልግሎት ለመስጠት ዕቅድ አለኝ» በማለት አስረድቶ ስለድርጅታዊ አገልግሎትም እንደሚከተለው ገልጧል ። ድርጅታዊ አገልግሎት በሱ አባባል የሰንበት ት ቤት አባል ሆኖ መንፈሳውያን ወጣቶችን ማስተማርና የሚያስፈልገውን አስተዋጽኦ ማድረግ መሆኑን ጠቅሶ ምናልባትም አሁን ያለው የሰበካ ጉባዔ አቋም ከተለወጠና በጥሩ ሁኔታ ከተሻሻለ በሰበካ ጉባኤ አባልነት ለመሥራትና ለማጠናከር ምኞትና ዕቅድ እንዳለው በመጠቆም በዚህ ሁሉ ራሱን መድቦ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ሙሉ ፈቃደኛ መሆኑን ገልጦ ፤ ከዚህ ሁሉ በይበልጥ ምግባረ ሠናይን የመሰለውን ክርስቲያናዊ ድርጅት ማጠናከር በጣም ደስ እንደሚለው አስረድቷል ።

ዲያቆን መንክር ቢተው ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻና የቅስናን ማዕረግ ስለ መቀበል ያለው አስተዋጽኦ እንዴት እንደሆነ ሲገልጽ ለክህነት የምትበቃ ፡ በመልካም እምነት የጸናችና ክርስቲያናዊ ሕይወቷም የተስተካከለ ሴት ማግኘት ከተቻለ ሥልጣን በመቀበሉ በኩሉ ችግር እንደማይኖር አረጋግጦ «ይህን የምለው የክህነትን ሥራ በተዛባ አስተያየት የሚሰጡ ሰዎች ስለማይጠፉ

ወደ ገጽ ፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

**መምህር ሠረገላ**

መምህር ሠረገላ በ18ኛው ምእት ዓመት ፍጻሜ ገደማ ተወለዱ የትውልድ አገራቸውም ሰቆጣ ነው ። መምህር የመጀመሪያ ትምህርታቸውን በተወለዱበት አካባቢ ከተከታተሉ በኋላም መምህር ተጠምቆ ወደተባሉት ስመጥሩ ሊቅ ጉባኤ ተዛውረው ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው ለመምህርነት ተመርቀው የመጻሕፍት ብሉያትን ትርጓሜ አጠናቅቀው አውቀዋል ።

የመጻሕፍት ሐዲሳትንና የመጻሕፍት ሊቃውንትን ትርጓሜ ተምረዋል መምህር ሠረገላ ዓይነ ሥውር ሲሆኑ በማስተማር ያበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በብዙዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ አድናቆትን አትርፎላቸዋል ከርሳቸው በትምህርት የተወለዱት ሊቃውንትም ትልቅ ዝናን አትርፈውላቸዋል ።

ሠረገላ በዓይነ ሥውርነታቸው ተስፋ ሳይቆርጡ ለትምህርት የነበራቸውን ከፍተኛ ትጋት እየተመለከቱ አስተማሪያቸው መምህር ተጠምቆ በትጋት ያስተምሩአቸውና ይረዱአቸው ነበር ።

በመሆኑም በፍጥነት ትምህርትን ለመከታተልና ለማወቅ የሚረዳ እንደ ጊዜው አነጋገር የቀለም አብነት አድርገውላቸው እንደነበር ይነገራል ።

ይህ ዓይነቱ አባታዊ ልግሥና የተደረገላቸው መምህር ሠረገላም አለመማርን ከታላቅ በሽታ ፣ መማርን ግን ከፍጹም ጤናማነት ቆጥረውት በዘረፉት መወድስ በስተመጨረሻው "ሕሙም ሠረገላ ተፈወሰ በተጠምቆ" ሕመምተኛው ሠረገላ በመጠመቅ ተፈወሰ" ብለው አስተማሪያቸውን በኅብር ቅኔ አድንቀዋል ።

እርሳቸው ራሳቸውም ከድንቁርና በሽታ ተላቀው የትምህርት ፈውስ ማግኘታቸውንና በሊቃውንት የክብር መድረክ ላይ መቆማቸውን አረጋግጠዋል ።

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ በቅኔ ሞያ እጅግ አድርገው ይመሰገኑ ስለነበረ አራት የቅኔ ደቀመዛሙርት መቱን አቁመው ለሚዘርፉላቸው ቅኔ ቤቱና ምሥጢሩን አስበውና ወስነው እንዲሰጡዋቸው ይጠይቁዋቸው ነበር ።

በሚሰጣቸው የምሥጢርና የቤት ውሳኔ መሠረትም ለአራቱም ደቀ መዛሙርት በየተራ አራት አራት መወድስ ይዘርፉ እንደነበር ይነገርላቸዋል ።

በዚህ ዓይነቱ አስደናቂ ሞያቸውም በጉባኤያቸው የሚገኙ ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይሆን በቅርብ የሚያውቋቸውና በሩቁ ዜናቸውን የተከታተሉት ታላላቅ ሊቃውንት ሁሉ እጅግ አድርገው ያደንቋቸው ነበር ።

በጐጃም የዲማ ተወላጅና ስለመዝገብ ድጓ ዐዋቂነታቸውም "ድጓልብሱ" ይባሉ የነበሩት ራቅ ማሠሬ ካሣ በቅኔ ዘረፋ ከመምህር ሠረገላ ጋር ለመወዳደር ቀርበውና የውድድሩም አሸናፊ እንደሚሆኑ ያለምንም ዓይነት ሥጋት አረጋግጠው ነበር ።

ቁመታቸው በጣም አጭር ስለመሆኑ ተማሪዎች "ካሣ ጉዱ" የሚሉዋቸው ራቅ መሠሬ ካሣ ከመምህር ሠረገላ የቅኔ ጉባኤ ተገኝተው በየበኩላቸው ወይም እርስ በርሳቸው ለመዛረፍ በተወዳደሩበት ወቅት መምህር ሠረገላ የተወሰኑላቸውን ምሥጢርና ቤት ሳያፋልሱና ሳያቋርጡ በቅደም ተከተል እስከአራትና አምስት መወድስ ለመዝረፍ ሲችሉ ራቅ ማሠሬ ካሣ ጉዱ ግን ሁለት መወድስ ብቻ ዘርፈው የቅኔው ንባብም ሆነ ምሥጢሩ ተጣ አለባቸው ።

የቅኔው ዘረፋ ውድድር አሸናፊ የሆኑት መምህር ሠረገላም ስለ ካሣ ጉዱ ተሸናፊነት

ወበጌጋያት ክልኤቱ ቃላተ መወድስ ንእስ

አክዓብ ካሣ ጉዱ እስከ ማዕዜኑ ተሐነክስ

አክዓብ ጉዱ ካሣ በሁለት የመወድስ ቃላት በደሎች እስከ መቼ ታነክሳለህ) የሚል መወድስ ቅኔ ወዲያውኑ ስለዘረፉባቸው ሊቃውንቱ በአድናቆት ላይ አድናቆትን አከሉ ።

በሊቅነታቸው የታወቁት የዋሸራው መምህር ተክሌ "በዘመኔ ካየኋቸውና በቅርብ ከማውቃቸው ሊቃውንት ሁሉ ለመምህር ሠረገላ ተወዳዳሪ የሚሆን አላጋጠመኝም" እያሉ ለትምህርታቸውም ሆነ ለምርምራቸው ከፍተኛ የሆነ ግምት ይሰጡት ነበር ።

አብዛኛውንም የጉባኤ ጊዜያቸውን ያሳለፉት በታላቁ ደብር በደብረ ማርቆስ ቅኔ በማስተማር ነው በሞያቸው የታወቁትን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የመንከባከብ ልምድ የነበራቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖት መምህር ሠረገላን በትምህርታቸውና በአስተዋይነታቸው "ባለህ እርጋ" ሳይሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያደርጉትና በሚያበረክቱት የምርምር አስተዋፅኦ በጣም ያመሰግኗቸውና ያከብሯቸው እንደነበር ይነገራል ።

የዕረፍታቸው ዕለትና ዓመት ተለይቶ ባይታወቅም ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዕረፍት በኋላ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ጐጃምን በሚያስተዳድሩበት ጊዜ እንደነበር ታሪካቸውን የተከታተሉት አረጋግጠዋል ቀብራቸውም የተፈጸመው በዚያው በደብረ ማርቆስ ነው ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## ደራሲ የመሆን ዝንባሌና መንሥኤው

ፈላስፋው ፕላቶን « የጥበብ መጀመሪያው ማድነቅ ነው » ይል እንደነበር ይነገራል ። ታዲያ ሰው የተፈጥሮን ውበት በማድነቅ ማን ፈጠረው ? ከምንስ ተገኘ ? ፍጻሜውስ ምን ይሆን ? እያለ መጠየቅ ሲጀምር በምርምር ያገኘውን ውጤት መጀመሪያ በሥዕል ቀጥሎም በጽሑፍ / ለማስፈር / ለመግለጥ እንደ ተነሣሣ ታሪክ ይናገራል ።

ስለዚህም ኢትዮጵያዊው ምሁር ዶ ር የማነ ገ/ ማርያም በጻፉት የፍልስፍና ትምህርት « ሰው በተፈጥሮው እውቀትን የማፍቀር ጠባይ አለው ፣ ከጥንት ጀምሮ የፍጥረትን ልዩ ምሥጢር ለመረዳት ጥረት ከማድረግ ቦዝኖ አያውቅም ፡ ይኸውም ትንሹንም ሆነ ትልቁን የማድነቅና ኋላም ምስጢሩን የማወቅ ፍላጎት በተፈጥሮው የተቀረጸበት በመሆኑ በሁሉም ነገር መጠየቅና መመራመርን ያፈቅራል ፣ ይህም በመሆኑ እነሆ ዛሬ ከምናየው ከፍተኛ የስልጣኔ ዕድገት ደረጃ ላይ ደርሶ እንመለከታለን፣ በዕውቀቱም አማካይነት በሥነ ፍጥረት ሁሉ ላይ ከፍ ያለ ሥልጣን በማግኘት ፍጥረት ራስዋ አገልጋይ ሆና ትታዘዛለች ለማለት ያስደፍራል » ። ሲሉ በትክክል አስቀምጠውታል ።

በሐዋርያት ሥራ 17 ፡ 21 « የአቴና ሰዎችና በዚያም የሚኖሩ የውጭ ዜጋዎች ሁሉ ሁልጊዜ አዲስ ነገር ከመናገርና ከመስማት በቀር ሌላ ፍላጎት አልነበራቸውም » የሚል ቃል በዘመነ ሐዋርያት ተጽፎ ይገኛል ።

ይህንንም ሰፋ ባለ ሃሣብ በመተንተን ኢትዮጵያዊው ሊቅ ዶክተር ዕጓለ ገዮሐንስ በፃፉት « የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ» ገጽ 17 እንዲህ ሲሉ ገልጠውታል ። «የአውሮፓን ሥልጣኔ የመሠረቱት አቴናውያን ናቸው ይባላል ይህንንም የሚናገረው ሌላ ሰው ሳይሆን ራሳቸው አውሮፓውያን ስለሆኑ ነገሩ ዕውነት ነው ። ታዲያ እነዚያ የጥንት አቴናውያን አንድ የመንፈስ ጠባይ ነበራቸው ። ይኸውም አዲስ የሆነ ነገር ለማየትና ለመስማት እጅግ የጠነከረ ፍላጎት ነበራቸው ፣ ስለዚህም አዲስ ትምህርት አዲስ ጥበብ አዲስ ፍልስፍና ይሰጣል ብለው የሚያምኑበትን ሰው ሲያገኙ ዛሬ እንደ አዲሱ ዘመን አጠራር ብሔራዊ ሸንጎ ወይንም ኮንግሬንስ ወዘተ ይመስላል ተብሎ በሚገመተው « አርዮስፋጎስ » እያሉ በሚጠሩት የሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ እየጋበዙ የማናገር ልምድ ነበራቸው ይህም ዕድል አንድ ዕለት ለሐዋርያው ጳውሎስ ደርሶት በዚያ አደባባይ ላይ ለመናገርና ለማስተማር መቻሉ ተጽፎዋል »

እንግዲህ ይህ ሁሉ አዲስ ነገርን የማድነቅ ዝንባሌ የሰውን ፍላጎትና ስሜት በማነሣሣት የተፈጥሮን ምንነት ለመረዳት የሚያደርገው ፍልስፍናዊና ሣይንሣዊ ምርመራ ሁሉ ተጠቃሎ የሚነደፈው በድርሰት መልክ መሆኑ አይካድም ።

ስለዚህም አንድን ሰው የደራሲነት ዝንባሌ ሊያሳድርበት የሚችል የተፈጥሮን ሒደት የማድነቅና የማወቅ ፍላጎት ነው ። «የማይታየው የእግዚአብሔር ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከአለም ፍጥረት ጀምሮ በተሠሩት ነገሮች ሁሉ ታውቆግልጥ ሆኖ ይታያል » ሲል ሐዋርያ ጳውሎስም የፃፈው ይህኑ በማስመልከት ነው። ሮሜ 1 ፡ 20-21

### የሥነ ጥበብ (ኤስቴታቲክስ) ልዩ ልዩ ክፍሎች

ኤስቴታቲክስ( [illegible] ) ማለት ድርሰትን የሥዕል አሠራርና የቅርፃቅርፅን ጥበብ የሚያስተነትን አጠቃላይ የንድፈ ሐሳብ(ቲዮሪ)ሥያሜ ነው። ስለርሱም ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ ሊኖረን የሚገባ አጭር ዝክረ ነገር በድርሰት በቅኔ ፡ በስዕል ፡ በማህሌትና በሽብሻቦ በሙዚቃና በዘፈን ፡ በድራማ በአጭር ታሪኮችና ልብ ወለድ አጻጻፍ የሰውን አእምሮ ለማነፅና ወደ ብሩህ ማስተዋል ለመምራት የሚያስችል ፍሬ ሐሳብና ትክክለኛውን የተፈጥሮ ውበት ለመግለጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁት የድርሰት የስዕልና የቅርፃቅርፅ ሥራ ውበት መከሠቻ ዋና ዋና ክፍሎችን በሚቀጥለው ሁኔታ በአጭር ትንታኔ በቅደም ተከተል ማቅረብ እንቀጥላለን ።

1 - መክሥተ ውበት ( የውበት መስታወት )

ውበት የሰውን መንፈስ የሚያድስና በፍሬ ነገሩ በመልኩና ባቀራረቡ ትንሽ ትልቅ ሳይባል ማንኛውንም ሰው በደስታና በአድናቆት የሚሞላ ወይም የሚያስገርም አስደንጋጭ ግርማ መልክዕ በመግለጥ ልብን የሚመስጥ ስሜትን የሚማርክ ኃይል ያለው የመንፈስን እርካታ የሚሠጥ አንድ ነገር ሠርተው የሚያቀርቡበት ክፍል ነው ። ይህም ዓይነት ተግባር እንዲህ በቀላሉ ማንም ሰው የሚያከናውነው ሳይሆን የተፈጥሮ ስጦታንና ልዩ አስተዋይነትን ከትምህርትና ከረዥም ጊዜ የሥራ ልምድ ጋር የተፈጥሮ ስጦታን ይጠይቃል ፡ ለሁሉም ወሣኝ ሙያ ነው ማለት ይቻላል ከፍተኛ ሙያ ያለው ሰው ትንሽና መናኛ የሆነውን ነገር እንኳ አጉልቶ የተለየ ቅርፅና መልክ ሰጥቶ የውበትና ግርማ መንሀባረቂያ ሊያደርገው ይችላል «ብልህ ሰው ሲይዘው ድንጋይ እንኳ ወርቅ ይሆናል » እንዲሉ ።

በባለሙያዎች የተጻፉ ድርሰቶችን የተዋቡ ምስሎችን የታነፁ የቅርፅ ሥራዎችን የተዘረፉ ቅኔዎችን የተዘፈኑ ሙዚቃዎችንና የሚታዩ ድራማዎችን

ወደ ገጽ [illegible] ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# በሲዳሞ ክፍለ ሃገር

## የጉጂ ብሔረሰብ ባህል

ባለፈው እትማችን በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በስድስቱም አውራጃዎች ውስጥ ተሰበጣጥረው የሚኖሩ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች መኖራቸውን ጠቅሰን ነበር ። ከነዚህም ብሔረሰቦች ጌዴኦ ፡ ሲዳማ ፡ አማሮ ፣ ኮይራ ጉጂና ቦረና ቡርጂ ፡ መርሐን ሎሳን ፣ ገረመሮና ዲጐዳይ የተባሉ እንደሚገኙ ዘርዝረናል ። እዚህ ላይ አበክረን ያመለከትነው የጌዴኦን ብሔረሰብ ባህልና ወግ መሆኑ ይታወሳል አሁንም ቀጥለን የምንጽፈው ደግሞ ስለጉጂ ብሔረሰብ ይሆናል ።

የጉጂ ብሔረሰብ በክፍለ ሃገሩ ውስጥ ከሚገኙ ዐበይት ብሔረሰቦች መሃል የሚቆጠር ነው ። ብሔረሰቡ በጐሣና በአሲቃ የተከፋፈለ ነው ። ጐሣዎቹ አቤቱ ፡ ዳንቱ ፡ ሜሪቱ ፡ ባለ ፡ ኳንጊቱ መኪንቱ እና አንእልቱ ተብለው በሰባት ይከፈላሉ ። የጉጂ ብሔረሰብ በክፍለ ሀገሩ መሃልና ዳርዳር ከወዲያ እስከ ባሌ ከወዲህ እስከ ጋሞጐፋ ይገኛል መተዳደሪያቸውም እርሻና ከብት ርባታ ነው ።

### ጋብቻ

ወጣቶች ለአቅመ መጠን ሲደርሱ የሚጋቡት በወላጆች ምርጫ ጭምር ነው ። ወጣቱ ሁኔታው ወደ ትዳሩ ሲያጋድል የልጁ አባት "ነገ እንግዳ ቤታችሁ ስለሚመጣ ወደ ሌላ ሥፍራ ሳትሄዱ ቤት ሁናችሁ ጠብቁ ብሎ የሚጠቁምና የሚያስጠነቅቅ ወጣት መልእክተኛ ይልክባቸዋል ። የልጅትዋ ወላጆችም በመልእክቱና በመላክተኛው አቋም ወይም ወጣትነት ልጃቸውን ለማጨት እንግዳ እንደሚመጣ አውቀው ተዘጋጅተው ይጠብቁዋቸዋል በማግሥቱ ሙሽራው በሚዜዎቹ ታጅቦ ወደ ልጅቱ ቤት ያመራል እዚያም እንደ ደረሱ ወደ ቤት እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ በተነጠፈላቸው ቁርበት ላይ ከልጅቱ አባት ጐን ይቀመጣሉ ወዲያው የልጅቱ እናት ወተት በጮጮ ካቀረበች በኋላ በጮጮው መክደኛ ቀድታ ለሚዜው ትሰጠዋለች ሚዜውም ይቀበልና ከጠጣለት በኋላ ቀጠል አድርጎ ለልጁ ያቀብልዋል እርሱም ጠጥቶ ሲያበቃ የተረፈውን ለልጅቱ ይሰጣታል ይህ በዚህ ካበቃ በኋላ የልጅቱ አባት ገድ አብሳሪ ወይም ወሬ ነጋሪ በብሔረሰቡ አጠራር ፈሮ የተባለው ወፍ ስለጋብቻው ምን እንደሚል የልጅቱን አባት እንዲያዳምጥ ካስታወሱት በኋላ ልጁ ካጃቢዎቹ ጋር ተሰናብቶ ወደ ቤቱ ያመራል ።

በበነጋው ወደ ልጅቱ ሌላ ጉዞ ይደረጋል ። ይህኛውን ጉዞ የሚያደርገው የልጁ አባት ነው የልጁ አባትም ተጉዞ ልጅትዋ አባት ቤት እንደ ደረሰ "ፈሮ" ወፉ ስለጋብቻው ጉዳይ ምን እንደተናገረ የልጅቱም አባት እንዲያወሳው ይጠይቀዋል "ፈሮ" ወይም ወፉ ስለጋብቻው የተናገረው መጥፎ ሁኔታ የሚያመለክት ሁኖ ከተገኘ የልጅቱ አባት "ፈሮ አልፈቀደም" ዳግመኛ ለዚህ ጉዳይ አትልፋ ይልና እቅጩን ይነግረዋል ባንፃሩ ግን ፈሮ ወፉ የጋብቻው ነገር ጥሩ ውብ እድል ነው ካለ የልጅትዋ አባት ለልጁ አባት "መለስ እያልህ ሳትሰለች ጠይቀኝ ይለዋል ደጅ ጥናቱ በዚህ ሁኔታ ይቀጥልና የልጁ አባት ከአራት ጊዜ በላይ ደጋግሞ ይመጣና ይጠይቃል ። በአራተኛው ጊዜ የልጂቱ አባት ለልጁ አባት "እስቲ በጉዳዩ ላይ ከዘመድ አዝማድ ጋር ልወያይበት" ይልና አሁንም በቀጠሮ ይመልሰዋል ። በሚቀጥለው ጊዜ እሽታውን ይገልጽለታል ቀጠሮም ይደረጋል በእለቱም ሌላ መልእክተኛ ወደ ልጂቱ አባት ቤት ተልኮ አሁንም የፈሮን የወፉን ድምፅ ሲያዳምጥ ያድራል ።

ሲነጋም ወደ ልጁ አባት ቤት ሂዶ የወፉን ንግርት ያጫውተዋል የልጁ አባትም ይህን ከሰማ በኋላ አሁንም ወደ ልጅቱ አባት ቤት ሄዶ በተሰጠው ተስፋ መሠረት ወፉ ምን እንዳለ ይጠይቀዋል ። የልጂቱም አባት በተደጋገመ ሁኔታ ስለልጁ መዳር ወፉ የነገረው የቀና ንግርት መሆኑን ሲያም ንበት ለልጁ አባት እንዲህ ሲል ይገልጽለታል "ልጅህ ልጄ ነው የእኔም ልጅ ልጅህ ናት" በማለት የልጁን አባት ደስ ያሰኘዋል ከዚያም እንደ ባህሉ ልጅትዋ እዚያ ወላጆችዋ ቤት እንድትቆይ ተደርጐ የልጁ አባት በተሰጠው ቃል ረክቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል ። ከዚህ በኋላ የሁለተወጣቶች ጋብቻ እስከ ተፈጸመ ድረስ ልጁ የልጂቱን እናት በአጋጣሚ በመንገድ ላይ ካየ ይደበቃል ። ልጅቱን ግን ለብቻዋ ካገኘ ይመታታል ወላጆችዋም ይህን ሲሰሙ ከቤት እንዳትወጣ ከወጣችም ከሰው ጋር እንዳትሄድ ያስጠነቅቋታል ። በዚህ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየች በኋላ ይደገስና ትዳራለች

በሠርጉ ዕለት ሙሽራው በፈረስ ሁኖ በሚዜዎቹ በሌሎችም ተከታዮች ታጅቦ ልጅትዋ ቤት ይደርሳል ። እዚያም ከተበላና ከተጠጣ በኋላ ሲመለሱ ሙሽራው በፈረስ ተቀምጦ ሲቀድም ሚዜው ሙሽራዋን በፈረሱ ላይ አፈናጦ ይከተለዋል ። ሠርገኞችም ልዩ ልዩ የባህል ዘፈኖችን እየዘፈኑ ሙሽሮቹን አጅበው ይገባሉ ።

### ኀዘን

በጉጂ ብሔረሰብ ዘንድ ህፃን የሞተ እንደሆነ ወላጆች ህፃኑ በሞተ በሦስተኛው ቀን እጃቸውን በቅቤ ያሹታል ትርጉሙም ሁለተኛ ልጅ እንዳይሞትባቸው ነው ። ከዚህ በኋላ ኀዘኑ ያበቃል ይህም በቅቤ የመለማመን ልምድ "ሚጨራቴ" ተብሎ በብሔረሰቡ ዘንድ ይታወቃል ። ነገር ግን ሟቹ አዋቂ ሰው ወይም የጐሣ አሊቃ ከሆነ ብዙ ከብት ታርዶ ይደገሳል ። ሟቹም ከፍ ባለ ኀዘን ይቀበራል ። ከዚያም የሟቹን ቤትና ንብረት በሙሉ ወንድሙ ይወርሰዋል ።

ስለጉጂ ብሔረሰብ ባህል በመጠኑ ያሳየን ሲሆን ብሔረሰቡ ባለው ጠቃሚ ባህል ውስጥ ሠርገው የገቡ ኦጉል ባህሎችና ልምዶች በመሠረተ ትምህርት ሂደትና በባህል ዘመቻው እንደሚወገዱ አይጠረጠርም ።



## ከዲቁና .....

ከገጽ ፭ የዞረ

ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ የሚስማሙ ልጃገረዶች በጣም ጥቂቶች ይሆናሉ ብዬ ስለምገምት ነው» ካለ በኋላ« ይህ የኔ አስተያየት ሲሆን (መልካም ሚስት ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት) ምሳ. 18 ፡ 14 እንደተባለው ሁሉ እግዚአብሔር ለእሱ የሆኑትን መርጦ እንደሚሰጥ እምነቱ ጽኑዕ ነው » ብሏል ።

በመጨረሻም ስለቤተ ክርስቲያን ውለታ ጠቅሶ «እንኳንስ ለኛ መንፈሳዊ ትምህርት ተምረን ለምናገለግላትና ለድኩማን ሁሉ መጠጊያ በመሆኗ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የበጎ አድራጎት ድርጅት ሆና እንደቆየች የማይረሳ የታሪክ ሀቅ ነው ። ሆኖም ለኔ አዲስ የሆነብኝ ይኸው ታሪክ በሕይወቴ በመፈጸሙ ነውና ዳዊት ስለ ኢየሩሳሌም እንደተናገረው ቤተ ክርስቲያን (ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ) እንድል መንፈሴ ያስገድደኛል » በማለት አስተያየቱን ደምድሟል ።

<u>ዲያቆን ወልደ ሥላሴ ይትባረክ</u>

ወልደ ሥላሴ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቅኔ ፣ ዜማና አቋቋም ያጠና ሲሆን በዚሁ መንፈሳዊ ዕውቀቱ ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ ዘመናዊ ትምህርቱን ቀጥሎ ከ1ኛ እስከ 11ኛ ክፍል በደብረ ዘይት ተከታትሏል ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ቀድሞ በነበረው የቅ . ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብቶ 12ኛ ክፍልን አጠናቋል ። ቀጥሎም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ዩንቨርስቲ ገብቶ ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ በማጥናት ትምህርቱን በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ሲከታተል ቆይቶ በ1973 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በማዕረግ በቢ.ኤ . ድግሪ ተመርቋል ።

ዲያቆን ወልደ ሥላሴ በነዚህ ዓመታት ውስጥ በትምህርት ላይ በነበረበት ጊዜና ከዚያም በፊት የቤተ ክርስቲያን ርዳታ ያልተለየው መሆኑን ጠቅሶ ፡ ደብረ ዘይት በነበረበት ጊዜ በዚሁ በደብረ ዘይት ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ተጠግቶ በመዘምርነት እያገለገለ በመኖሪያ ቤትና በመሳሰለውም ሁሉ ከሞላ ጎደል በቤተ ክርስቲያኒቱ ሲረዳ መቆየቱንና አዲስ አበባ መጥቶ በመንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ በነበረበትም ወቅት በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ከተቋቋመው ከዚህ ኮሌጅ በሚያገኘው ርዳታ እየተጠቀመ 12ኛን ክፍልን መፈጸሙን አመልክቶ « በአጠቃላይ ዘመናዊውን ትምህርት ለመማር ድጋፍና ምክንያት የሆነችኝ ቤተ ክርስቲያን ናት » በማለት ከማስታወሱም በላይ ወደ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ከፍተኛ ትምህርቱን በሚከታተልበት ጊዜ እንኳን የሰንበት መምህር በመሆን እንዲያስተምር ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ስለተፈቀደለት በትርፍ ጊዜው እያስተማረ በሚያገኘው መጠነኛ ገንዘብ እየተረዳ ትምህርቱን መጨረሱን አስገንዝቧል ።

በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ስላደረገችለት ውለታ ፡ ዲያቆን ወልደ ሥላሴ ሲገልጥ « ዘመዶቼ ከህፃናት ስለነበሩ ከህፃንነቴ ጀምሬ ያደግሁት በቤተ ክርስቲያን በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ለእኔ ያደረገችው ርዳታ በዚያው መጠን ብዙ ስለሆነ አንድ ባንድ ለመዘርዘር ያሸቸግራል » ብሏል ቀጥሎም እሱ ወደፊት ለቤተ ክርስቲያን ሊሰጥ ስለሚችለው አገልግሎት ሲያስረዳ «በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ሙሉ ፈቃድ አለኝ ። የአገልግሎቱ ሁኔታ ግን እንደኔ ችሎታና እንደቤተ ክርስቲያኒቱ ፍላጎት ሊወሰን ይችላል ። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር እስከፈቀደ ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ባለኝ ችሎታ ለማገልገል ያለኝ ፍላጎት የማይገታ ነው ። ይልቁንም በቅኔ ማኅሌት የሚያገለግሉ ብዙ መዘምራን ስላሉ እኔ ወጣቱን ክፍል በመንፈሳዊ ትምህርት ለመርዳት ስለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖቱን የበለጠ እንዲያውቅበ ማጠናከር መሥራት የበለጠ ደስ ይለኛል» ብሏል ።



ስለ ሕጋዊ ጋብቻ ያለውን አስተሳሰብም እንዲነገግረን ጠይቀነው እስከዛሬም እንዳሰብኩትና እንደኔ ምኞት ሳይሆን እዚህ የደረስኩት በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ አሁንም ፈቃዱ የእግዚአብሔር ነው » በማለት ሃሳቡን አጠቃሏል ።

## ደራሲ የመሆን ...

ከገጽ ፯ የዞረ

በመመልከት አድማጮችንና ተመልካቾችን የሚማርክ ውበትና ጸጋ የሚኖራትው ስለዚህ ነው ።

ለምሳሌም ይላሉ ዶ ር የማነ ሥነ ጽሑፍን በሚመለከት ፍልስፍና ትምህርት በተሠኘው መጽሐፋቸው ቅፅ 2 የግብጽ ፒራሚዶችን የቻይናን ግንብ ፡ የኒዮርክ ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎችን እንደ ብሮክሊን ያሉ ከፍተኛ ድልድዮችን ወይም ደግሞ ከሥነ ፍጥረት ክፍሎች በተለይ እንደኒያጀራ ያሉትን ታላላቅ ፏፏቴዎች ከሃገራችንም የዐባይን ፏፏቴ በመጨመር በውቅያኖስ ውስጥ የሚነሣ እንደ ከፍተኛ ማዕበል ሞገድና ግፊት የበዛበት ውሽንፍር ወጨፎ ወይም በባሕርም በአየር አንድ ከፍተኛ እልቂት የተፈፀመበትን ድርጊት ማለትም በመንግስታት መካከል የተደረገ አደገኛ ጦርነት የመሳሰሉትንም ሁሉ በምንመለከትበት ጊዜ በመጀመሪያ የሚገጥመን ሁኔታ ፍርሃትና ጭንቀት የሞላበት የመሸበር ስሜት ይሆናል የራሣችን ሃይልና የሰውነታችን መጠን አነስተኛ ከመሆኑ የተነሣ ከአቅማችን በላይ የሆኑ የተፈጥሮ ለውጦች ንቅናቄዎች ሲፈጠሩ የኃይላቸውንና የግዙፍነታቸውን መጠን ከብደቱን ተመልክተን ከነርሱ ጋር የምንወዳደርበት አቅም የሌለን መሆናችንን እና መዛዝናለን ነገር ግን እየተለማመድናቸው ስንሄድ አድናቆትና ድፍረት እየተሠማን መደነቅ እንጀምራለን ።

ቁ መክብብ አጥናው

www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከዚህ የሚከተሉትን አቅርቤአለሁና መልሱ ተብራርቶ ይመለስልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ ፤ ጥያቄዎቹም ፡- 1ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስትሆን አስተዳደሩዋ ግን የተለያየ ሆኖ እናያለን ፤ ታዲያ ቤተ ክርስቲያንዋ አንዲት ስትሆን አስተዳደርዋ ለምን አንድ እንዲሆን ጥረት አይደረግም ?

2ኛ በየአህጉረ ስብከቱም ያሉ አስተዳደሮች እንዲሁ የተለያዩ ናቸው ፤ መንበረ ጵጵስናው እነዚህን የተለያዩ አስተዳደሮች አንድ አድርጎ ካልመራ የመንበረ ጵጵስናው ዓላማ ምን ይሆን ?

ቤተ ክርስቲያን የምትመራበት ሕግ ‘‘ቃለዓዋዲው’’ ሲሆን ለምን በሥራ አይተረጐምም ? ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች መልሳቸው ከመፍትሔው ጋር ተብራርቶ በዓምድህ ይገለጽልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ ።

ፀጋው ገብረ ሥላሴ
ከአዲስ አበባ

ፀጋው ገብረ ሥላሴ ያቀረቡት ጥያቄ ተፈላጊና ወቅታዊ ስለሆነ የሚደገፍ ነው ። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስትሆን የተመሠረተችውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደም ነው ። ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረችበት ጊዜ ጀምሮ ሐዋርያት ይመሩዋት ና ያስተዳድሩዋት የነበረው ፣ በአንድ ፍጹም ሕግ ነው ይኸውም ፍጹም ሕግ ሕገ ወንጌል ሲሆን በዚህ ሕግ ሌሎች ሕግጋት ይጠቃለላሉና ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትም ሕገ ወንጌልን ምርኩዝ አድርገው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሕገ ሲኖዶስ እንድትመራና እንድትተዳደር አድርገው ቤተ ክርስቲያን በአንዲት ሃይማኖት ፣ በአንድ ሕግ ፣ በአንድ አስተዳደር ፣ በአንድ ሥርዓት ስትተዳደር ኖራለች ።

አመራሩዋና አስተዳደሩዋም በኢየሩሳሌም በተደረገው የሐዋርያት ጉባዔ ተመክሮና ተወስኖ በተላለፈው ሕግና ሥርዓት ይመራና በማኅበረ ምእመናኑ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ በተመረጡ ቅዱስ መንፈስ ባደረባቸው ኃላፊዎች ሥራ አስፈጻሚነት ይካሄድ ስለነበረ የሚፈጸመው ሥራም መንፈስ ቅዱስን ደስ የሚያሰኝ ነበረ ። ግን ያን ጊዜ የተመረጡት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መቃናት መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው ፣ ለሃይማኖት የታዘዙ ክርስቲያኖች እንዲበዙ የሚጥሩ ስለነበሩ ሥራቸው ሁሉ የተቃና እንዲሆን የምርጫው ውጤት የጸሎት መልስ በመሆኑ ዕውነተኛ ምርጫ ነበረና በጠቅላላው ነዚህ ቅዱሳን የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሆኖ አል ።

ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ለአንድነቲዋና ለዕድገትዋ ለአስተዳደርዋም እንቅፋት የሚሆኑ አላውያን ቢገጥሟትም በየጊዜው የሚነሱ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና አባቶች አንድነትዋ እንዲጠበቅ ፣ ሃይማኖትዋ እንዲጸና ፣ አስተዳደርዋም እንዲቃና በሚያደርጉት ጥረት አላውያኑን አውግዘው ከህደታቸውን አስወግደው ፣ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ፀንቶ ሳይናወጥ እንዲኖር አድርገዋል ።

በእንዲህ ዓይነት ዘመናት መካከል አቋርጣ ከእኛ ጊዜ የደረሰችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሌላው የበለጠ በአሁኑ ጊዜ የገጠማት ችግር ቢኖር የአስተዳደር ጉዳይ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሁንም የምትመራው በሲኖዶስ ሲሆን የተለያየ ችግር እንዳለባት ስንመለከት አስቸኳይ መፍትሔ እንደሚያስፈልጋት አያጠያይቅም ። የዛሬው የቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያንዋ በተሐድሶ እንድትራመድ እድገትዋም ከምዕመናን ጋር ሳይነጣጠል እንዲራመድ ጥረት እያደረገ መሆኑ አይዘነጋም ።“

ከዚህም የተነሣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚጠቅሙ የተለያዩ ደንቦችን በማውጣት ላይ ሲገኝ ከነዚህ ደንቦችም በተቀዳሚ የሚጠቀሰው ማኅበረ ምእመናን ለማደራጀትና ለማጠናከር ተሻሽሎ የወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ ‘‘ቃለ ዓዋዲ’’ ነው ።

ይህ ደንብ መላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ዓይነት አስተዳደር በአንድ አመራር እንድትተዳደር ታስቦ የወጣ ሲሆን ደንቡ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የቅድሚያ ዝግጅት ባለመኖሩ በብዙ ቦታዎች ችግሩ እየጐላ ሄዶአል ።

ምክንያቱም 1ኛ ደንቡ ከመውጣቱ በፊት ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ተልኮ በተለይም አካባቢንና አፈጻጸሙን በሚመለከት ረገድ ግምገማና ትችት ያልተደረገበት በመሆኑ ለአፈጻጸሙ ችግር ስለ ፈጠረ ።

2ኛ ደንቡ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በደንቡ የሰለጠኑ ሰዎች እየተዘዋወሩ የጥቂት.ቀናት ገለጻ እንዲያደርጉ ባለመደረጉ ፤

3ኛ ደንቡ እንደወጣ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ካህናት ስለደንቡ አፈጻጸም የተሰጠ ሴሚናር ገለጻ ካለመኖሩ የተነሳ ደንቡና የደንቡ ፈጻሚዎች ስለማይተዋወቁ እንዲሁም ደንቡ በምእመናንና በካህናት ዕጅ በብዛት እንዲደርስ ባለመደረጉ እና የመሳሰሉት ሁሉ ተደራርበው ሕጉ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ያደረጉ ይመስላል ።

በዚህም ምክንያት በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚፈጠረው ጭቅጭቅ በአሁኑ ጊዜ እየበረታ ከመሄዱም በላይ ሌላው ታላቁ ችግር ግን በዚሁ ደንብ መሠረት በተቋቋሙት የሰበካ ጉባኤ አባላትና በአስተዳዳሪው እንዲሁም በምእመናንና በካህናት መካከል በሚፈጠረው አለመግባባት ያለው አስከፊ ውዝግብ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚታየው አለመግባባትና ውዝግብ እጅግ አድርጎ የሚያሳስብ ነው ።

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ያለው አስተዳደር እንደ የአብያተ ክርስቲያናቱ ቁጥር የተለያየ ነው በመሆኑ ሁሉም ያውቀዋል በአንዳንዶቹ አብያተ ክርስቲያናት የደብሩ አስተዳዳሪ በሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር በመመራት እርሱ ካለው አይወጣም እርሱ ያዘዘውን ብቻ ይፈጽማል አንዱ ዲያቆን ጤና እንደማይሰጥ ተቆጥሮ ከሥራ ሲወጣ ሌላው እንደ ደጋፊ ታይቶ ደመወዝ ይጨመርለታል ሊቀ ዲያቆን ይሆናል ከዚያ በኋላማ ካህናቱን ከምንም ባለመቁጠር መብታቸው ሲረገጥ አድማው ከቤተ መቅደሱ ይቆሰቆስና የቤተ ክርስቲያኑን አጥቢያ ያጥለቀልቀዋል ። በሌላዋ አጥቢያ ቤተ ክስርስቲያን ደግሞ የሰበካው ጉባዔ ሊቀ መንበር ከአፈጮሌ ካህናት ጋር ይገጥምና አለቃው ስለአስተዳደር እንደ ማያውቁና በአስተዳደርም በኩል ሥልጣን እንደሌላቸው ሥልጣኑ ግን ለሰበካ ጉባኤው ብቻ እንደሆነ በመገመት ያስተዳዳሪው ደጋፊዎች ወይም ቀራቢዎች ናቸው የሚባሉትን ካህናት በመቅጣት ከሥራ በማስወጣት ፣ በአጠቃላይ ከመንፈሳዊ ሥነሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ ቤተ ክርስቲያንዋን ምዕመናን እንዲርቋት ሲያደርጉ ይታያል ።

በዚህም ምክንያት ምእመናን ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዳታዘዘ በመቁጠር ያችን ቤተ ክርስቲያን ትተው ሌላ ሩቅ አጥቢያ ያለች ቤተ ክርስቲያን በመፈለግ ሲንከራተቱ ከመመልከት ሌላ ለቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች የሚያሳዝን ምን ነገር አለ ?

በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ በጣም የሚያስገርም ነገር አለ ይኸውም የቃለ ዓዋዲው ደንብ አንድ የሰበካ ጉባኤ አባል በድጋሚ ካልተመረጠ በቀር መሥራት የሚችለው ለሁለት ዓመታት ብቻ መሆኑን ሲወስን አንዳንዶቹ ግን ይህንኑ ደንብ በመተላለፍ በድጋሚ ሳይመረጡ ከአምስት ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ ከመቆየታቸውም በላይ ምርጫ ይካሄድ ሲባል እንዲህ ዓይነትዋን ነገር የተናገረውን ሰው በማሳደድ አድመኛ ነው ከሥራ ይባረር ፣ የቤተ ክርስቲያን ንብረት ዘርፎአል ። ቤተ ክርስቲያንዋን ሳያቃጥላት ይባረር በማለት ያልሆነ ውዥንብር እየፈጠሩ ግራ በማጋባት ሥልጣናቸውን ለማራዘም ይፍጨረጨራሉ ።

ይህ ብቻ አይደለም አዲስ የሰበካ ጉባኤ አባላት እንዲተኩ የሰበካ ጉባኤው ደንብ በሥራ እንዲተረጐም ጥረት ሲደረግ ከእነርሱ በቀር ለቤተ ክርስቲያን አስቦ የሚሠራ ክርስቲያን ፈጽሞ የሌለ በማስመሰል እኛ የጀመርነውን ሥራ ሳንጨርሰው ከሄድን ሥራው ተጀምሮ በከንቱ መቅረቱነው ። ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ ካለኛ አይፈጸምም ሥራውን እንድንጨርሰው የምርጫው ቀን ይራዘምልን ፣ በማለት ማመልከቻ ሲጽፉ ደጋፊዎቻቸውን በማንጋጋት በማሳደም እንዳይነሱ ብላችሁ ፈርሙ ፤ እያሉ እንደቀድሞው የፓርላማ ምርጫ በግብግብ በጉቦ ፤ ምእመናንንና ካህናትን ግራ ሲያጋቡ መመልከቱ ምን የተለየ ጥቅም ያገኙ ይሆን ? ወይስ ለቤተ ክርስቲያን አስበው ይሆን ፤

አንዳንድ የነቁ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች እንዲህ አይነቱን የከፋ አድራጐት ሲቃወሙ ደግሞ ለጉዳዩ የሚያገባቸውን ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ አድባራት ሥራ ፈተው የሚንገላወዱትን ጭምር በማጠረቃቀም ጥቂት የጽሑፍ ፊርማዎች እንዲፈረም ከተደረገ በኋላ በጣት ፊርማዎች ሲለቀልቅ ውሎ እንዲያም ሲል የፈጠራ ስም እና ፊርማ ተጨማምሮበት በጥቂት ሳንቲሞች የተገዙ ቦዘኔዎች ስልፉን ያንጐደጉዱታል ። የቤተ ክህነት ግቢ ትጨነቃለች ከዚህ በኋላማ በአለቃው ላይ ካህናቱና ሕዝቡ አድመውበታል ይነሳ የዲስፒሊን ጉባኤ ያጣራው አጣሪ ኮሚቴ ይቋቋም ይባላል ።

. ግን ከነዚያ ውስጥ ከደብሩ የመጣችሁ ምእመናንና ካህናት መታወቂያችሁን አሳዩ ቢባል በቁጥር የሚሞሉ ግለሰቦች እንደማይገኙ ከዚህ ቀደም በተደረገው ተደርሶበታል ታዲያ እገሌ ይሠራልና አይነሳብን በመባል ፊንታ የሥራ ጊዜያችን ይራዘምልን ፤ ልንሻር አይገባንም ማለታቸው አቅጣጫው ምንን ይመስላል ?

ለነገሩማ ከቃለ ዓዋዲው ሕግ በላይ በአንድ ጊዜ ምርጫ ከአምስት ዓመታት በላይ የሠሩ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ምክትል ሊቀ መንበር “የሰበካ ጉባዔው ደንብ ገና ወደፊት የሚሻሻል ስለሆነ



www.ethiopianorthodox.org

"ደንቡ እስከሚሻሻል ከምክትል ሊቀ መንበርነቱ ልነሳ አይገባኝም" ብለው አቤቱታ አቅርበዋል ይባላል ታዲያ ይህ ሁሉ ትንቅንቅ ለምን ይሆን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ይሆን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚያስቡ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን የጥልና የንትርክ ቤት እንድትሆን ማድረጉ ዕድገትዋንም ማደናቀፍ እንጂ ማሻሻል አይደለምና ለዕድገቱዋ የሚያስቡላት ከሆነ "ከነገሩ ጦር ምዕደሩ" ነውና የሰበካ ጉባኤው ደንብ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ቢረዱ የተሻለ ነበር ።

በየአህጉረ ስብከቱም ቢሆን እንዲያውም የቃለ ዓዋዲው ደንብ ያልደረሰቻው አብያተ ክርስቲያናት ስለሚበዙ በወጣው ቃለ ዓዋዲ ደንብ አንዱዋ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ዓይነት አስተዳደር እንድትመራ ካስፈለገ ደንቡን ሁሉም ያጥኑት እንላለን ።

ሌላው ተጨማሪ መፍትሔ ይሆናል ብለን የምናምንበት 1ኛ የሰበካ ጉባኤ አባላት በ2 ዓመታት ብቻ እንዲወሰኑ ሲደረግ የሰበካ ጉባኤ መምሪያ የሥራ ጊዜያቸውን ፈጽመው የሚሰናበቱበትን ዕለት መምሪያው ተቆጣጥሮ አዲስ አባሎችን ቢያስመርጥ ኖሮ ከገደቡ አልፈው የሰበካ ጉባዔ አባላትም ባልተንዛዙ ነበር ።

2ኛ የ14ቱም ክፍላተ ሀገር የሰበካ ጉባኤ ምርጫ በአንድ ቀን ቢሆን ፡ ይህም ባይቻል የአዲስ አበባ አድባራት ምርጫ አንድ ቀን ቢሆንና የየክፍላተ ሃገሩንም በአንድ ቀን ማስመረጥ ባይቻሉም እንኳ የየራሳቸውን አህጉረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ አባላት ምርጫ አንድ ቀን ቢያደርጉ ከሁለት ዓመት ምርጫ ወደ ስድስት ዓመት ባልተራዘመም ነበር ።

ስለዚህ የሰበካ ጉባኤ መምሪያ በጥብቅ ቢያስብበት መልካም ነው ።

3ኛ የሰበካ ጉባኤ አባላት የጊዜ ገደብ ለ2 ዓመታት እንዲሆን እንደተወሰነ ሁሉ የደብር አስተዳዳሪዎች በአንድ ደብር መቆየትም ገደብ ቢኖረው እንዲህ ዓይነቱን ንዝንዝ ሊያቆመው ስለሚችል ስለዚህ ጉዳይም የሚመለከተው ክፍል ትኩረት ቢሰጠው መፍትሔ ይሆናል በቸልታ እንዳይመለከተው ያስፈልጋል ።

4ኛ አንድ የደብር አስተዳዳሪ ከተሾመበት ደብር አጠፋ ጉድለት ፈጸመ ፡ ተጋለጠ ተብሎ በብዙ ጭቅጭቅ ከተነሣ በኋላ ጉዳዩ በትክክለኛ ፍትሕ ተጣርቶ ማጥፋት አለማጥፋቱ መረጋገጥና ውሳኔ ማግኘት ሲገባው አድማው ሲበዛ ፡ ግርግሩ ሲያስቸግር ከአንድ ደብር ተነስቶ በአቅራቢያው ወዳለው ደብር ይቀየራል ፡ ታዲያ ይህ ምን መፍትሔ ሊሆን ይችላል? እንዲህ ዓይነት ልማድ ስለበዛ በየቦታው አጥፍቶ የተቀጣ ሙሌ ዲያቆን በሚጭረው አድማ ከፍተኛ ብጥብጥ ይፈጠርና ቤተክርስቲያንዋ በአድማ ትጥለቀለቃለች ። ስለዚህ የሚነሳው አስተዳዳሪ የፈጸመው ጥፋት ያደረሰው ጉድለት በትክክል ተጣርቶ ሲታወቅ ቢነሳና እንዲህ ዓይነቱም አስተዳዳሪ ደግሞ በአስተዳዳሪነት እንዳይመደብ ቢደረግ ፡ እንዲሁም የአንድ ደብር አስተዳዳሪ ተከስ በተጨባጭ ሁኔታ ጉድለቱ ተጣርቶ በትክክል ከተደረሰበት በኋላ እንደገና በሌላው ቦታ እንዲሾም ካንዱ ያጠፋውን ወዳንዱ በማለዋወጥ መተካት "ጉልቻ ቢቀየር ወጥ አያጣፍጥም" እንደተባለው ነውና በሽታው እንዲጋባ ከማድረግ በቀር የሚሰጠው ጥቅም ስለሌለ ፡ ሳያጠፋ አድማ ፈርቶ መቀየር ካጠፋ በኋላ ከብሩ እንዳይነካ ያህል ወደሌላው ደብር መቀየር ቢቀር መልካም ይመስላል ።

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አንዳንድ የስም ካህናት ከወንጌል ትምህርት ውጭ የሆነ "መርበብተ ሰሎሞን፡ መፍትሐ ሥራይና መፍትሔ ሀብት" የሚባሉ ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸውን ልፋፎች እንደግማለን ሀብት እናስገኝላችሁአለን ፤ ከሕማማችሁም እንፈውሳችሁአለን በማለት የዋሁን ሕዝብ ያታልላሉ ። በዚህም አድራጎታቸው ክርስቲያኑን ሕዝብ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ጣዖት ይመራሉ ። ብዙ ጊዜም የሚያታልሉ ሴቶችን ነው። እንደ እነዚህ ያሉ አታላዮች ከዚህ ማታለላቸው እንዴት ሊታረሙ ይችላሉ።

ለማና ጓደኞቹ
የፖ.ሣ.ቁ.1641
አዲስ አበባ

ለማና ጓደኞቹ ያቀረባችኋቸው ጥያቄዎች ለጊዜው እጅግ በጣም አንገብጋቢዎችና ተፈላጊዎች ናቸው ።

ለጤንነትም ሆነ ለሀብት እንዲሁም ለሌላ ችግር የሚበጁ መድኃኒቶች ያሏቸው ሰዎች ካሉ ወደጤና ጥበቃ እየሄዱ ዕውቀታቸውን ቢገልጹ ይመሰገናሉ እንጂ አይነቀፉም ይህንንም ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየጊዜው ያሳስባል ነገር ግን ይህንን ቻል ብለው መርበብተ ሰሎሞን እየደገሙን መፍትሔ ሥራይ እናደርጋለን መፍትሔ ሀብት ስላለን የደኸየውን ሰው በአስማታችን በሥራያችን እናከብራለን ፣ የታመመውንም ቢሆን ለማዳን እንችላለን በማለት እያታለሉ የሰውን ሀብት የሚነጥቁ አታላዮች ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ቅጣት ተዘጋጅቶ የሚጠብቃቸው መሆኑን በቅድሚያ ሊያውቁት ይገባል ሕዝብም ቢሆን ያውቁልኛል ብሎ ወደ እነርሱ ሄዶ ከመጐናበስ ይልቅ አታላይነታቸውን በይፋ ማጋለጥ አለበት ።

እነዚህ አታላዮች ለሌላው መፍትሔ ሀብት እናውቃለን ይላሉ እንጂ ራሳቸው ጠም አዳሪዎች ናቸው ሌላውን እንፈውሳለን ሲሉ ራሳቸው በሽተኞች ሆነው ሲጨነቁና ሲማቀቁ ይታያሉ ።

ታዲያ እንደዚህ ያሉ በሽተኞች እንደነዚህ ያሉ ድሃዎች ያድኑኛል ያበለጽጉኛል ብሎ ወደ እነርሱ መጠጋት ማስ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# ብቻህን አትሂድ

የሐዋርያት ጥሪ ደርሶአቸው የሚላኩ ፡ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰማሩ በአጠቃላይ በጎ አድራጎትን ሁሉ ለማከናወን በየሥፍራው የሚዘዋወሩ ሁሉ ባልንጀራ ሳይዙ መሄድ እንደማይገባቸው በፍጥረታት አፈጣጠር ለመረዳት ይቻላል ።

እያንዳንዱ ፍጥረት የሁለትነት ባህርይ አለው ጥንድ ጥንድ ሆኖ ያልተፈጠረ ምንም ነገር የለም በሕዋሳት በኩል ብንመለከት ሙሉ ሰው የሚባለው ሁለት ጆሮዎች ሁለት እጆችና ሁለት እግሮች ሲኖሩት ነው ከእነዚህ ሕዋሳት ሁሉ አንዱ ቢጐድል ሥራው ሁሉ በሚገባ አይከናወንለትም ።

ይህ ከሆነ ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ብቸኛ መሆን የለበትም ባልንጀራ ያስፈልገዋል መካሪና ጎረቤትም ያሻዋል ። ይህ ችግር እንዳለ የተመለከተው ሰሎሞን "ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሳዋልና አንዱ ብቻውን በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሳው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት" ሲል ብቸኝነትን ተቃውሞ ሁለት መሆንን ግን ደግፎ ጽፎአል መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 4 ቁጥር 9 - 10 ።

እንዳለውም ከብቸኝነት ሁለት መሆን ይሻላል መባሉ ከባልንጀራ ብዙ ነገር ስለሚጠበቅ ነው ይኸውም ብቸኝነት ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ሲሆን በሁለት መካከል የሚፈጠር ባልንጀርነት ግን በደስታም ሆነ በመከራ ጊዜ እውነተኛ ፍቅርና የልብ ርዳታ የሚገለጽበትና የሚታይበት የብርሃን መቅረዝ ተመሳሳይ ስለሆነ ነው ።

ይህንንም ተግባር ሰዎች እንዲጠቀሙበት በመንፈስ ሲገልጽ የኖረውና አስቀድሞም ቃል የነበረው ሰውን ለማዳን ወደዚህ ዓለም መጣ ፡ በዚህም ዓለም በሚመላለስበት ወቅት ያለ ስብከተ ወንጌልና ያለ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን መሠረት እንደማይጸና ስላወቀ የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ከመጣሉ በፊት የሐዋርያትን ጥሪ ለማስተላለፍና ፡ የስብከተ ወንጌልን ተግባር ለመጀመር ሁለት ሰዎችንም መጥራት ጀመረ ። ሁኔታውም እንዲህ ነበር "በገሊላ ባሕር ሲመላለስ ሁለት ወንድማማቾችን ጴጥሮስንና እንድርያስን ዓሣ ለማጥመድ መረባቸውን በባሕር ላይ ሲጥሉ አየ መረባቸውን ትተው እንዲከተሉት ጠራቸው እነሱም መረባቸውን ትተው ተከተሉት ከዚያም አለፍ ብሎ ሌሎችን ሁለት ወንድማማቾች ያዕቆብንና ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በታንኳ መረባቸውን ሲያበጁ አየ ። ጠራቸውም እነርሱም ወዲያው ታንኳይቱንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት" የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ቁጥር 18 - 22 ።

ሐዋርያት ሁለት ሁለት እየሆኑ መጠራት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ለስብከተ ወንጌል አገልግሎትም ሁለት ሁለት እየሆኑ መላክ የሚያሻ መሆኑን ክርስቶስ በተግባር ገልጾት እናገኛለን ምክንያቱም አንዱ ሲወድቅ ሌላው እንዲያነሳው አንደኛው ሲደክም ሁለተኛው እንዲያጽናናው በማለት ነው ስለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ጊዜ 12ቱን ደቀ መዛሙርት ጠርቶ ደዌንና ሕማምን እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጥቶ ላካቸው ቀጥሎም የመዳንን ቃል እየተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ በፀጋ የተቀበሉትን በፀጋ እንዲሰጡ የሰላም መልክተኛ ሆነው ስለ ሰላም እንዲመሰክሩ "ሌሎችን ሰባ ደቀመዛሙርት ሾመ ። ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው" የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 1 ።

ሁለት ሁለት ሆነው የተላኩትም ተግባራቸውን ፈጽመው በደስታ ተመለሱ አጋንንት እንኳን ሳይቀሩ ስለተገዙላቸው ጌታን አመስግነዋል ይህም በሁለት ባልንጀራ መካከል ያለውን መረዳዳትና ለሕዝብ የሚቀርብን አገልግሎት አጉልቶ ያሳያል ።

ይህ ሁሉ የታተተበት የሐዋርያት ጥሪ ደርሶት የነበረውን ፤ ሁለት ሁለት እየሆኑ ከተላኩት መካከል ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት አንደኛ ሆኖ የተላከውን የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በያመቱ ጥቅምት 12 ቀን የእረፍቱን በዓል በፀሎትና በቅዳሴ የምታስውስለትን ፤ የወንጌላዊውን የማቴዎስን የሥራ ታሪክ ባጭሩ ለመግለጽ ነው ። የቀድሞ ስሙ ሌዊ ይባላል ። ትውልዱም አይሁዳዊ ሲሆን ነገዱ ከነገደ ይሳኮር ነው ። አባቱም እልፍዮስ ይባላል ሥራውም ቀራጭ ነበር ።

እሱም በሮም መንግሥት አስተዳደር ለሥራ ተጠርቶ የቀረጥ ሥራ እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው በሚሠራበትም ወቅት ከፍ ያለ የገንዘብ ገቢ በሳጥን የማከማቸትና ፤ ከትንሹም ከትልቁም ጋር የመግባባት ልምድ ስለነበረው በየጊዜው ብዙ ደምበኞችን ይስብ እንደነበር ይነገርለታል ። ይህንንም የሚያውቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጠፉትን ነፍሳት ወደእግዚአብሐር መንግሥት እንዲሰበስብና ብዙ አሕዛብንም የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንዲያደርግ ተቀምጦ ወደ ነበረበት ወደ መቅረጫው ስፍራ ሄዶ ተከተለኝ አለው የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ቁጥር 9 ።

እሱም ሁሉን ትቶ ስለተከተለና ክርስቶስን አምኖ ስለተቀበለ ሌዊ የተባለው ስሙ ተለውጦ ማቴዎስ ተብሎ ተጠራ ። የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 3 እንደ ሊቃውንቱ አተረጓጎም ማቴዎስ ማለት ሀብት ማለት ነው የማቴዎስንም ወንጌል የጻፈው እሱ ነው።

ጽፎ ከጨረሰም በኋላወንጌልን ለማስተማር ወደ ልዩ ልዩ ሀገር ሄዶአል በየትአገር እንዳስተማረ እንዴት እንደሞተ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም ።

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን አባት የሆነው አውሳብዮስና ሶቅራጥስ ወደ

ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ጥንታዊትዋ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ሕፃናቱን እየሰበሰበች በቅጽርዋ ግቢ ማስተማርዋንና የልማት ሥራዋን እያካሄደች ባለማቋረጥ እስካሁን ድረስ መሥራትዋ አይካድም ።

ረክባ ወላጆችን በመወከል ስብሰባ በትምህርት ተንከባክባ ለማሳደግ ሥራዋን ታካሂዳለች ።

ትንሣኤ ፤ ለሕፃናቱ የሚሆን አስፈላጊው ዝግጅት ማለት ልብስ ፤ ቀለብ ይህ የመሳሰለውም ሌላ ሁሉ ማን ነው የ



ቄስ እሸቱ ምሕረቱ የሕጻናት አስተዳደግ ጉባኤ ረዳት ዋና ጸሐፊ



ተማሪዎቹ ድጓ ሲማሩ

1ኛ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሊቀ መንበር

2ኛ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ አባል

3ኛ የሕፃናት ማሳደጊያ ዲሬክተር ዋና ጸሐፊ

4ኛ በመንበረ ጵጵስና የተመረጡ 2 ሰዎች አባላት

5ኛ በሕፃናቱ አስተዳደር ጉባኤ የተመረጡ ሁለት ሰዎች አባላት በመሆን ባለው ውስጠ ደምብ መሠረት ሥራውን ይመራሉ ።

ትንሣኤ ፤ የሕፃናት ማሳደጊያው ድርጅት ስንት ዓመት ያላቸውን ሕፃናት ይቀበላል ?

ቄስ እሸቱ ፤ ድርጅቱ የሚቀበላቸው

ሀ አባትና እናት ያጡና ፍጹም ድኆች የሆኑትን

ለ ወላጆቻቸው በሕይወት ቢኖሩም በአካል ጉድለት ወይም በሌላ ምክንያት ሊረዱአቸው ያልቻሉአቸውን

ሐ/ የተረጂው ሕፃን ዕድሜ ከ7 ዓመት በላይ ከ14 ዓመት በታች

መ በትምህርት በኩል ከ8ኛ ክፍል በታች

ሠ/ የሕፃኑ ጤንነት በሐኪም የተረጋገጠ የሆነውን ነው

ትንሣኤ የሚረዱት ሕፃናት ፍጹም ድኆች ለመሆናቸው የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ምንድን ነው ?

ቄስ፡- በቀበሌና በገበሬ ማህበራት እንዲሁም በሕዝባውያን ድርጅቶች አስመስክረው ያስመሰከሩበትን ደብዳቤ ሲያቀርቡ ነው

ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦ.ቤ. ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር በምታደርገው መንፈሳዊ ግንኙነትና ከእነርሱም በምታገኘው እርዳታ ረዳትና አሳዳጊ የሌላቸውን ሕፃናት ለማሳደግ በየክፍላተ ሀገሩ አዳሪ ት ቤቶችን እያቋቋመች ሥራዋን ጀምራለች ይህንንም መሠረት በማድረግ የሕፃናቱ ማሳደጊያ እንዴት እንደተቋቋመ ቄስ እሸቱ ምሕረቱን አነጋግረናቸዋል ።

ትንሣኤ ፤ ይህ የሕፃናቱ ማሳደጊያ እንዴት ሊቋቋም ቻለ ?

ቄስ እሸቱ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባላት መልካም ግንኙነትና ተሰሚነት በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ በሰው ሠራሽና በመሳሰሉት ምክንያቶች ያለ ተንከባካቢ የቀሩትን ድኀ አደጎች ሕፃናት ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ተ


ሚችለው ?

ቄስ እሸቱ ፤ ለሕፃናቱ ቀለብና ልብስ እንዲሁም ጠቅላላ ባጀት በምዕራብ ጀርመን ውስጥ ኬንደርኖት ሂልፍ እየተባለ ከሚጠራው ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት የሚገኝ ርዳታ ነው በዚህ በሚገኘው እርዳታ ለጊዜው በወሎና በትግራይ ክፍላተ ሀገር በደረሰው ድርቅ ምክንያት ጀመርን ከዚያም በኋላ ድርቁም ጦርነቱም ባጠቃቸው ክፍላተ ሀገር አስፈላጊውን ጥናትና ዝግጅት እያደረግን እስካሁን ድረስ በርከት ያሉ ሕፃናትን በመሰብሰብ በ 18 አዳሪ ቤቶች እየተቀበልን እናሳድጋለን ።

ትንሣኤ ፤ ድርጅቱ እንዴት ባለ አመራር ነው የሚመራው

ቄስ እሸቱ እነዚህ አዳሪ ቤቶች የሚተዳደሩትና የሚመሩት በኮሚቴ ነው ። ኮሚቴዎቹም የሚከተሉት ናቸው ።





ሕጻናቱ በወሎ ደሴ ከተማ በአቡነ ጴጥሮስ የሕጻናት ማሳደጊያ ከቦርድ አባላት ጋር



በጀርመን የሕጻናት ርዳታ ዋና ጸሐፊሚ/ር ሉዶር ሉዎርል ኬ ኩርዝ ከጐንደር ሐ ጳውሎስ ት/ቤት ልጆችን ሲያነጋግሩ



www.ethiopianorthodox.org

ትንሣኤ ፡ - በዓመት ውስጥ ስንት ሕፃናት ትቀበላላችሁ ?

ቄስ ፡ -በዓመት ልንቀበላቸው የምንችለው ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ምን ያህል አዳዲስ ሕፃናት

ለ ለሕፃናቱ ማሳደጊያ አመች ቦታና በቂ ቤት መኖሩን ስናረጋግጥ

ሐ ለልጆቹ ትምህርትና ጤንነት ምቹና ተስማሚ ቦታ ሆኖ ስናገኝ እንደተፈቀደልን መጠን ልጆችን

ንፈሳዊ ጥበብ እየተገነቡ በዘመናዊ ዕውቀትም እየታነጹ ካላደጉና ዕውቀቱም አብሮአቸው ካላደገ የሀገርና የወገን ፍቅር አያድርባቸውም የነፃነትንም ክብር አያውቁም የሃይማኖትም ጽናት አይ



በጎጃም የፈለገ ዐርዝ ት ቤት ተማሮች ሲያርሱ

መቀበል እንዳለብን ሲፈቀድልን ብቻ ነው ይኸውም በዓለም ውስጥ አንደኛ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው 40 ሀገሮች ጋር ተመልክቶ ይህን ያህል ሕፃናት ተቀበሉ ሲለን እኛም በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ክፍላተ ሀገር

ሀ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ቅድሚያ ይሰጣል ።

እንቀበላለን የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ቤቶችንም እንከፍታለን በዚህ መሠረት በዚሁ በያዝነው ዓመት አዳሪ ት ቤት እንድንከፍትላቸው የጠየቁ ነበሩ ግን በአንዳንድ ቦታ ብዙ በሌላ ደግሞ ጥቂት ሕፃናት ስለሚገኙ የተወሰነው መጠን እስከሚስተካከል ሁሉም በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ ።

ሕፃናት በሕፃንነታቸው ወቅት በመኖራቸውም በጠቅላላ የሥጋዊውንም ሆነ የመንፈሳዊውንም ተግባር ሊገነዘቡ አይችሉም ፡ መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን ጥበብ አስተባብረው ይዘው ካደጉ ግን ክፉውንና በጎውን የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ነገር ሁሉ ለይተው ስለሚያውቁ ሀገራቸውን የሚወዱ ሃይማኖታቸውን የማይክዱ ወገንን የሚያከብሩ ይሆናሉ ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ



# ክርስቲያን በተስፋ

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው በገነት
ሁሉን ሰጥቶ ነበር ያለምንም ጉድለት
ነገር ግን አንዲቱን ዕፀ በለስ በልቶ ፤
እንዳይሞት ነገረው ድንገት ተሳስቶ ።
እንዳለው አልቀረም አዳም ተሳሳቶ
ያችን በለስ በልቶ የሞት ሞትን ሞቶ ።
ውጣ ከዚች ገነት ውረድ ወደ ምድር
በላብህ በወዝህ ጥረህ ግረህ እደር
የሚል ቃል ደረሰው ከፈጣሪው እግዜር
አዳም አልዘገየም ጥፋቱን ተረዳ
በጣምም አዘነ ሰውነቱን ጐዳ ።
ፈጣሪን ለመነው ይቅር እንዲለው ፤
ወደ ጥንት ቦታው እንዲመልሰው ።
ቸር አምላክ ነውና እርሱም አዘነለት
በማይሻር ቃሉ ቃል ኪዳን ገባለት
መልሶ ነገረው እንደዚህ በማለት
አሁን አይቻልም ገነት ልትመለስ ፤
የመዳንህ ዘመን እስኪመጣ ድረስ
ምንም አልጥልህም ፈጣሪህ ነኝና
አንተን ለማዳን ስል እያለሁ ፈተና ።
ሥጋዬን ቆርሼ ደሜንም አፍስሼ
አስቀምጥሃለሁ በገነት መልሼ
ጊዜው በመርዘሙ አዳም ሳይከፋ
ደስ ብሎት ጠበቀው የመሢሁን ተስፋ
ተስፋው ይፈጸም ዘንድ መድኅን ተወለደ
በመስቀል እስኪሞት በፍቅር ተገደደ
ለእኛ ለሰው ሲል ሰጠን ትልቅ ተስፋ
በደሙ ከታጠብን ፍጹም እንዳንጠፋ
በእምነት በተስፋ በፍቅር ጸንተን
ላይኛውን አገር ለመውረስ ተስፋ አለን
ያ የአዳም ተስፋ ለእኛ የሞተው
መስቀል ተሸክሞ የተንገላታው
ኑ ወደ እኔ ይላል እኔን ተከተሉ
የዘለዓለም ሕይወት እንድትቀበሉ
ስለዚህ ክርስቲያን ይኖራል በተስፋ
በልቡም ይረዳል ፈጽሞ እንዳልጠፋ
ታጥቦም ስለ ነጻ በክርስቶስ ደም ፤
በሥጋ በነፍስም እድፍ የለበትም
በሰማይ ቤት አለኝ ብሎ ስለሚያስብ ፤
ያልደከመበትን ምንም አይሰበስብ ።
የሰይጣንን ሥራ ፈጽሞ እያጠፋ
ዘለዓለም ይኖራል ክርስቲያን በተስፋ ።
ጥልና ክርክር የለም በእርሱ ቤት
ይቅርታንም ያውቃል አለው ቸርነት
አይሽቀዳደምም ሹመት ለማግኘት ።
ብቻ ግን አይተውም ጌታውን ማመስገን
ምን ጊዜም አይረሳም የአምላክ ውለታውን ፡
ዘወትር ንቁ ነው ከቶ አያንቀላፋ
ሲያስታውስ ይኖራል የሰጠውን ተስፋ
አጣምሮ ይይዛል እምነትን ከሥራ ፤
ዕውነትን ሲናገር ጥቂትም አይፈራ
ምኞቱ ነውና መኖር ከአምላክ ጋራ
የሰውን ፊት አይቶ ማዳላት አያውቅም ፤
መስሎ ለመኖርም ከቶ አይታለልም ።
ትጉህ አገልጋይ ነው ታታሪ ገበሬ ፤
ሁልጊዜ ያመርታል የሕይወትን ፍሬ ።
ዓለም ብትኳኳል እጅግ ብትዋብም ፤
እርሱን ለማታለል ሌት ተቀን ብትደክም
ምኞትዋ ውድቅ ነው አይሳካላትም ።
ሰይጣንም ቢነሣ በሐሰተኛ ምክር
ክርስቲያን ጽኑዕ ነው ምንም አይበገር ።
ጌታን በመውደዱ ሰው ሁሉ ቢጠላው
ድኅነት ፤ በሽታ ጦር እንኳ ቢከበው
ሞት እጁን ዘርግቶ መጣሁብህ ቢለው
ከክርስቶስ ፍቅር ማንም አይነጥለው ።
የጌታንም ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ
ኗሪ ነው ዘለዓለም ተነግሮአል በቃሉ
ክርስቲያንም ያምናል ይህን የወንጌል ቃል
አያወላውልም ምርጫውንም ያውቃል
ለጊዜው ብቻ ሳይሆን አርቆ ያስባል
ዘለዓለማዊውን ሕይወት እንዲወርስ ይሠራል ።
አምላክ እስኪመጣ ሊፈርድ ለምእመናን ፤
ክርስቲያን በተስፋ ይፈጀል ጊዜውን ።
እኛስ ወገኖቼ አለን ወይ ? ይህ ተስፋ
በእምነትስ እንሠራለን ፍጹም እንዳንጠፋ
ሁለት ምርጫ አለን አንዱን ልንቀበል
እሳት ወይስ ውሃ የትኛው ይሻላል ?
በእሳት መቃጠል ወይስ በውሃ መታጠብ
የቱ ይሻል ይሆን አጥብቀን እናስብ
ቀጠሮ ሳይበዛ ነገ ዛሬ ሳንል ፤
የሁሉን መድኃኒት አሁን እንቀበል

ከባህር ዳር ከተማ ተማሪ ዳንኤል ክብረት



www.ethiopianorthodox.org

## ብቻህን ....

ካነጽ ፲ የዞረ

ኢትዮጵያ መጥቶ ወንጌልን እንዳስተማረና በሰማዕትነትም እንዳረፈ ጽፈዋል ። በይበልጥ ደግሞ ሞሬዬ የተባለው የፈረንሳይ ሊቅ ስለ ኢትዮጵያ በጻፈው መጽሐፍ በ393 ገጽ "ሌዊ ወይም ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት ከአምስቱ ሐዋርያት ይልቅ እሱ በጣም የታወቀ ነበር" ይላል ታሪኩን እንዲህ እያለ ይዘረዝራል ። "በፍልስጤም ብዙ ሰው አስተምሮና ወንጌልን አሳምኖ ከጨረሰ በኋላ እንደገና የወንጌልን አገልግሎት ለማዳረስ ወደ አፍሪካ ክፍል ተጓዘ በተለይም ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ መርዌ በምትባለው ከተማ ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክቶአል ። ወንጌልንም እያስተማረ በክርስቶስ ብዙ ሰው አሳምኖአል ።

ቅዱስ ማቴዎስም ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ያን ጊዜ ከነበሩት በለሥልጣኖች ጋር ስለ ተዋወቀ ሥራው ይከናወንለትነበር ይሁንእንጂ ከሁለት አስማተኞች ዘንድ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር እነዚህም አስማተኞች ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ሰውን በምትሐት እየሳቡ አድማጭ ለማሳጣት ስለሚሞክሩ ነበር በመጨረሻም እነዚህ አስማተኞች ሁለት ታላላቅ ዘንዶዎችን በአስማት ስበው ሕዝቡን ያስፈራሩት ጀመር ። ወንጌላዊው ማቴዎስም ክርስቶስ ሁለት ሁለት እያደረገ በላካቸው ጊዜ ዘንዶውን ፣ እባቡን ፣ ጊንጡን ፣ ብትረግጡ ምንም አይነካችሁ ባለው ቃል መሠረት እነዚያን ዘንዶዎች የማይናከሱ ለማዳዎች አደረጋቸው በዚህ ጊዜ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ አመኑ ያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ አካጥታህ ይህንን አስደናቂ ሥራ ስላየ ከነቤተሰቡ አምኖና ተጠምቆ የክርስቶስ ቤተሰብ ሆነ በመጨረሻም በትምህርቱ ብዙ የጣዖትን መቅደስ ካፈረሰ በኋላ በዚሁ አገር በሰማዕትነት እንዳረፈ ታሪክ ይደመድማል ።

እንዲህ ያለውን ሁኔታ ጠለቅ ብለን የተመለከትን እንደሆነ ወንጌላዊውን ማቴዎስ እውነተኛ ሐዋርያና ስሙን ሕያው አድርጎት የሚኖረው በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ስለሞተ አይደለም ስሙን ሕያው አድርጎት የሚኖረው ግን በዚያን ዘመን የነበረውን የዓለምን መጥፎ አስተሳሰብና አጉል እምነት በትምህርቱ ስለደመሰሰ ፣ አሮጌውን ሕይወት ወደ አዲስ ሕይወት ስለለወጠ የሞራል ውድቀትን በመንፈስ ንቃት ስለቀሰቀሰ ፣ የወንጌልን ብርሃን በጨለማ ለሚኖሩ ሕዝቦች ስላበራ ነው ። በዚህ አኳኋን ቤተ ርክስቲያናችን ስለ መልካም ስራውና ትቶት ስላለፈው ቅርስ መጋቢ ዘመን አድርጋ ሾማ በየአራት አመቱ ታስበዋለች የጻፈውንም የክርስቶስን ወንጌል በምታስተምርበት ስፍራ ስሙን ትጠራለች ።

እንግዲህ ወደ እራሳችን ሕይወት መለስ እንበልና በአርስቱ ብቻህን አትሂድ የሚል እንደተጠቀሰ እናስታውሳለን እኛንም ሁለት ሁለት ሆነን ለአገልግሎት እንድንሰማራና እራሳችንን ለወንጌል ስብከት እንድንመድብ ክርስቶስ ይጠራናል ። የሚጠራንም ሌላውን ለማገልገል እንጂ በጌትነት ፣ በምቾት ፣ በአስተዳደር ላይ ቁጭ ብለን እራሳችንን እያዝናናን ፣ እራሳችንን እንድናገለግል አይደለም ፤ ይሁን እንጂ ይህንን ጥሪ የዘነጋን ጥቂቶች አይደለንም ለአገልግሎቱ ሌሎች ይጨነቁበት የምንል እየበረከትን ሄደናል ።

ይህንን ችግር የተመለከተችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማንን እልካለሁ ? እያለች እንደማቴዎስ ያለ ጠንካራ ወንጌላዊ ጠዋት ማታ ትጣራለች ። ጥቂቶቻችን ጥሪውን ስንቀበል ፣ በርከት ያልነው ደግሞ በውስጡዋ የሚገኘውን ፍሬ መመገብና በረከቱዋን ለመቀበል እጃችንን መዘርጋት ደስ ይለናል ። በምዕመናን መካከል ግን ተገኝተን ቅዱስ ቃሉን ማስተማር እናፍራለን ። ቤተ ክርስቲያንም ታፍርብናለች የማይሠራንም እጅ መዘርጋት ታላቅ በደል ነው ።

ምን ጊዜም ቢሆን የቤተ ክርቲያን ዓላማ ስብከተ ወንጌል በመሆኑ ሁለት ሁለት እየሆን ለአገልግሎት እራሳችንን በሐዋርያነት መመደብ ይገባናል ሐዋርያነት አንድ አቅጣጫን ብቻ የሚመለከት ይመስለን ይሆናል ። ሐዋርያነትም ማለት ወንጌልን ማስተማርና ቅዳሴ መቀደስ ብቻ አይደለም ። ወደልማት መሰማራት ፣ ረሐብን ፣ በሽታን ድንቁርናን ፤ የሞራል ውድቀትን ፣ አጉል ባህልን ከሰው ልጆች አእምሮ ለማስወገድ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ነጥለን ልናየው አይገባንም ። ስለዚህ የወንጌል መልክተኞች የሆንን ሁሉ እንደ ወንጌላዊው ማቴዎስ በየስፍራው እየተዘዋወርን በየስጦታችን ተመድበን ማገልገልና የጨለማ መብራት መሆን ይፈለግብናል "ሁለት ሁለት አድርጌ እልካችኋለሁ ሂዱና አስተምሩ" ተብሎአልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



### ወደ ምድረ ግብጽ መሰደድ

፲፫እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ ፣ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ፦ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ ፣ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ ፣ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው ። ፲፬-፲፭እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ ፦ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት የተባለውም እንዲፈጸም ወደ ግብጽ ሄደ ፣ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ ።



### ከምድረ ግብጽ መመለስ

፲፱ሄሮድስም ከሞተ በኋላ ፣ እነሆ ፣ የጌታ መልአክ በግብጽ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ፦ ፳የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ፣ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለ ። ፳፩እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ ። ፳፪በአባቱም በሄሮድስ ፋንታ አርኬላውስ በይሁዳ እንደ ነገሠ በሰማ ጊዜ ፣ ወደዚያ መሄድን ፈራ ፤ በሕልምም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ ፤ ፳፫በነቢያት ፦ ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ፣ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

በዚች ሰው አልባ ሆና በተፈጠረች ዓለም "ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉ አት ግዙአትም" የሚለውን አምላካዊ ቃል መመሪያ በማድረግ ከአንድ ወደ ሁለት ከሁለት ወደ ሶስት እየተጨመረ የሄደው ሰብአዊ ዘር ዓለምን አሁን ባለ ችበት ሁኔታ በሰው ዘር እንድትሞላ አድርጓታል ወደፊትም ይቀጥላል ። እን ግዲህ ያ "ብዙ ምድርንም ምሉአት ግዙአትም"የሚለው አምላካዊ ቃል አዎ ንታዊ በመሆኑ ዓለም ሕዝብ በሙሉ ወደደም ጠላ በዚህ ትእዛዝ ሥር መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ። ዓለም በሕዝ ብ ተመልታለችና ነው ።

ስለዚህ ኑሮአቸውን በቅዱስ ጋብቻ መሥርተው ካሉት አባቶች መካከል አንድ ሆነው ሊጠቀሱ የሚገባቸው አለቃ ሲራክ ፈቃደ ሥላሴ በዚህ እትም እንዲቀርቡ ሆነዋል ።



አለቃ ሲራክ ፈቃደ ሥላሴ

አለቃ ሲራክ ከነጋድራስ ፈቀደ ሥላ ሴና ከወ/ሮ ትደግ ብሩ በ1901 ዓ.ም. መጋቢት 29 ቀን ተወለዱ አባታቸው እርሳቸውን ከመውለዳቸው በፊት በኢየ ሩሳሌም ገዳም ዮርዳኖስ ውስጥ በምናኔ ብቻ ሳይመነኩሱ 12 ዓመት ከቆዩ በኋላ ዘር እንደልጓም ይስባል እንደሚባለው ከእግዚአብሔር ነገር አግኝተው ወ ሮ ትደግ (ወለተድንግልን) አግብተው ሁለት ሴት ልጆች ከወለዱ በኋላ አለቃ ሲራክንወለዱ ። ዳሩ ግን ከስምንት ዓመ ት በኋላ ያው ትዝታቸው ምናኔ ስለሆነ እንደገና ንብረታቸውን ትተው ደብረ አባይ ከሚባል ገዳም ገብተው ከመነ ኩሱ በኋላ ልጃቸን አምጡልኝ ብለው አለ ቃ ሲራክን በገዳሙ ውስጥ እንዲማሩ አድርገዋል ። አለቃ ሲራክም የግእዝን ንባብ ፈጽመው ጽዋትወ ዜማን የቅዳ ሴንም ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ አዲስ አበባ መጥተው ከአቡነ ማቴዎስ ዲቁናን ተቀብለዋል ። በዚህም ቤተ ክር ስቲያንን እያገለገሉ ደግሞ እንደገና የአቋቋምን ባህልና ቅኔን ከነአግባቡ ተምረው ተመርቀዋል ። ከዚያም የሐዲ ሳትና የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ከሐዲስ ተክሌ በኋላ አቡነ ዮሐንስ ተምረዋል ።

"መምህራቸው የጋብቻን ሥርዓት እንዲፈጽሙ ቢጠይቁአቸው አለቃ ሲራክ ለብዙ ጊዜ መልስ ሳይሰጡአቸው ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ እንደሚመነ ኩሱ ቢነግሩአቸው "የእግዚአብሔር ትእዛዝ ምንኩስና ሳይሆን በሕግ ተወ ስኖ መኖር ነው" ብለው ስለ አስገደዱ አቸው ፈቃዳቸውን ለመፈጸም በ1925 ዓ.ም. ወ ሮ ሙሉ ወርቅ ይትባረክን በተክሊልና በሥጋ ወደሙ አገቡ ። ከጥ ቂት ጊዜም በኋላ የውጪ አገር ነፃ ትም ህርት በመንግሥት ትእዛዝ መጣ ቅድ ሚያውም ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋ ወደሙ ለፈጸሙ ነበር ሌላው ቀርቶ ይላሉ አለቃ ሲራክ ሽልማትና የገንዘብም ስጦታ ይደረግ ነበር ። እኔም ሁለቱንም ለማግኘት ከአንኮበር ድረስ መጣሁ ። ውጭ ሄጄ እንድማር መንግ ሥት ስለፈቀደልኝ እሺ ስል መምህራ እዚያው ስለነበሩ አይሆንም ሕግ ገብ ቷል ብለው መልስ ሲሰጡ ምን ሕግ ይገባል ቀጨት እንጂ ተባለ ወዲያውም ለመሆኑ ምን ምን ተምሯል የሚል ጥያቄ ቀረበ መምህሬም ዘርዝረው ተና ገሩና በጽሕፈት ሚኒስቴር የሚያስፈል ገኝ ሁሉ እየተደረገልኝ እንዳገለግል ተፈቀደልኝ ። በዚያም ለሶስት ዓመታት ያህል እንዳገለገልኩ የትምህርት ሚኒስ ቴር ባልደረባ ሆኜ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ የእንግሊዝኛና የሒሳብ ትምህርት በማስተማር እንዲ ሁም ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት ላይ እያለሁ በቤተክህነትም ውስጥ የአ ዳሪና የተመላላሽ ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም እዚያው በማገልገል በደብረ



የአለቃ ሲራክ ባለቤት ወ/ሮ ሙሉ ወርቅ ይ ትባረክ እኒህ ነበሩ ።

ብርሃን ውስጥ የሚገኘው ከሳቴ ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ት/ቤት ውስጥ ልዩ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



# ይህንን ያውቁ ኖርዋል ?

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4ኛው ም ዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ የተነሣው ታላቁ እስክንድር እርስ በእርሳቸው ተ ለያይተው የነበሩትን የግሪክ አውራጃ ዎች በእርሱ መሪነት ሥር አንድ እንዲ ሆኑ ካደረገ በኋላ ሁለት ሀግቦች ከፊቱ ተደቀኑ ። አንድ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ገና የነበረው የፋርስ መንግሥት ቀድሞ ጠ ንካራ ኀብረት አጥተው መመከት ባል ቻሉበት ወቅት እየነጠለ እንዳንዳቸው ን በመምታት በግዛቱ ላይ የደረባቸው ን የግሪክ አውራጃዎች ነፃ ለማውጣት ሁለት እሱ ራሱ ተከትትኩቶ ያደገበትን የግሪክ ሥልጣኔ በዓለም ላይ ለማስፋ ፋት የምድር ነገዶችንም ሁሉ በአንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ተጠ ቃለው እንዲመሩ ለማድረግ ነበር ። በ ውስጡ ግን ጥበበ እግዚአብሔር ነበረ በት ትንቢት አስቀድሞ ተነግሮለት ነ በርና ያ ግድ መፈጸም ነበረበት

እርሱ ይህን ቢያውቅም ባያውቅም ተልእኮውን ለማድረስ ፊቱን ወደ ምሥ ራቅ ባቀና ጊዜ በመንገዱ ላይ የገጠመ ውን የፋርስ ጦር እያከታተለ ድል ያደ ርገው ጀመር፡፡በመጨረሻም ከጦር ሜዳ ንጉሠ ነገሥቱ ዳርዮስ በሰረገላው ተጋ ብቶ ሲያመልጥ እስክንድር ከዚያ አስ ቀድሞ በፋርስ መንግሥት ሥር ይገዙ የነበሩትን ሀገሮች ለማሳመን ወደ መካ ከለኛው ምሥራቅ ዞረ ሶርያ ወርዶ ደ ማስቆን ቀጥሎም ሲዶናን አሳመነ ። ጢ ሮስ ግን « ... እንዲያው ጉልበት እየተ ሰማው ልግዛችሁ እያለ ለመጣ ሁሉ አ ሜን ብዬ ስገብር ልኖር ? አይደረግም ለዳርዮስም አልሆንለት ..... ብላ ትከሻ ዋን አሳበጠች፡ታላቁ እስክንድርም ው ሎ ሳያድር ወዲያውኑ ዘመተባት ግን በባሕር የተከበበ ከተማዋን ዘሎ ገብ ቶ ለመያዝ ብዙ ጊዜ ወሰዶበታል ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታላቁ እስክንድ ር ወደ ምድረ እስራኤል መልክተኛ ይ ልካል ለሊቀ ካህናቱ ለጃዱዋ ። « የቀ ድሞ ገዥህን ዳርዮስን ድል አድርጌ መ ጥቻለሁና ለእርሱ ታገባ የነበረውን ግ ብር ውለህ ሳታድር እንድታገባልኝ ፡ ለሠራዊቱም የሚያስፈልገውን ቀለብ ና ስንቅ እንድታቀርብ » ብሎ ሊቀ ካሕ ናቱ ሲመልስ ከዳርዮስ በቀር ሌላ ገዥ እንዳይኖረው ፡ እርሱ በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበትም ዘመን ሁሉ ክንዱን እን ዳያነሳበት ለዳርዮስ ዕኑ መሐላ የማለለ ትና ዕኑ ቃል ኪዳን የገባላት በመሆኑ የእስክንድርን ጥያቄ ሊፈጽም የማይ ችል መሆኑን ገልጾ መልክተኞቹን ይ መልሳቸዋል ። ታላቁ እስክንድር ይህን ሲሰማ ቁጣው ይበረታል ። ለሌሎቹ መቀጣጫ ሳላደርጋት ብቀር ሰውየው እኔ አይደለሁም ብሎ እሳት ለብሶ እሳ ት ጐርሶ ወደ ምድረ እሥራኤል ይገሠ ግሳል ። እግረ መንገዱን ጋዛን እጅ አድ ርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ማቅናቱን ሊቀ ካህናቱ ሲሰማ ፡ ሊመክቱት ሊቋቋሙ ት የማይችሉት ጠላት ስለመጣበት ይ ጨነቃል ፡ የሚያደርገውን ያጣል ። ስ ለዚህ መጥቅዕ መትቶ ሕዝቡን ይሰበስ ባል ። « ማቅ ለብሳችሁ ፡ በራሳችሁ አመድ ነስንሳችሁ እዘኑ አልቅሱ ምሕ ላ ያዙ ፡ ይላቸዋል ። ከሕዝቡ ጋር መሥ ዋዕት ያቀርባል ። ሌሊቱን ራእይ ያያ ል ለምሕላውና ለጸሎቱ መልስ ያገኛል « አትፍራ » ይለዋል ሌሊት በሕልሙ ተገልጦ ፡ አትፍራ አትደንግጥ ምንም የሚደርስባችሁ ነገር የለም ። ከተማይ ቱ ትጽዳ የቅጽሯም በሮች ይከፈቱ ። ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ሀአዳ ፡ ሀአዳ ልብ ሱን ፡ ካሕናቱ እንደ የማዕረጋቸው ል ብሰ ተክሕኖአቸውን አንተም ሊቀ ካ ህናቱ የክብር ልብስህን ለብሳችሁ ው ጡና እስክንድርን ተቀበሉት - ምንም አያደርጋችሁም » ይለዋል ። ሲነቃ ባ የው ራእይ አመነ። ደስ አለው። ፍርሃቱ ጭንቀቱ ተወገደለት ። ስለዚህ በተነገ ረው መሠረት የንጉሡን መምጣት ተዘ ጋጅቶ ይጠብቅ ጀመር ።

ይህ ከሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታላቁ እስክንድር ወደ ከተማይቱ እየቀረበ የ መምጣቱ ዜና ተሰማ ። ሊቀ ካሕናቱ ም ሕዝቡን አሰልፎ ፡ ካሕናቱን አስከ ትሎ ሊቀበለው ወጣ ። ሁለቱ ወገኖች ገና ባሻገር ሲተያዩ ቆይተው እየተቀራ ረቡ ሲመጡ ያልታሰበ አንድ ነገር ድ ንገት ተፈጠረ ። እስክንድር ከፈረሱ ዱብ - ብሎ. ወርዶ ፈጠን ፈጠን እያለ በመራመድ - በችኮላ - ሊቀ ካሕናቱን ቀርቦ በአክብሮት እጅ ሲነሳው በማየ ታቸው የጦር ሹማምንቱ ይደንቃቸዋ ል ። ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነባቸው ። ከ መቼ ደርሼ ያ ፀቡይ ሊቀ ካህናት የሚ ገባበትን ጉድጓድ አይቼ ብሎ ዝቶ እን ዳልመጣ ሁሉ አሁን ነገሩ ሁሉ ተለው ጦ እንዲህ ሆኖ ሲያገኙት ታዲያ ምን ይበሉ ? በዚህ ጊዜ ፓርሜኒዮ የተባለ - ባለሟሉ ቀርቦ ፡ ንጉሥ ሆይ ይህ የምና የው እንግዳ ነገር ምንድነው ? እንዴት ስ ሊሆን ቻለ ? እንዴት ነው ላንተ የሚ ገባውን ክብር ለእርሱ የሰጠኸው ?

«ሰማህ?» አለ እስክንድር ሲመልስለት ይህንክብር የሰጠሁት እኔ አይደለሁም ይህን ክብር የሰጠው ፡ ከወገኖቹ መካ ከል አልቆ - ቀብቶ- ለዚህ ማዕረግ ክ ሕነት ያበቃው እግዚአብሔር ነው ።

ይገርምሃል ገና ከሀገሬ ሳልነሳ መቄዶ ንያ ውስጥ ዲዮስ በሚባል ቦታ ሳለሁ መላውን የእስያ ግዛት እንዴት ባደርግ ነው ጠቅልዬ በእጄ ላገባ የምችለው ? እያልኩ በልቡናዬ ሳወጣ ሳወርድ ቆ ይቼ እንቅልፍ ይወስደኛል ። ከዚያ በኋ ላ ምን እደሆንኩ ልንገርህ ? ይኸውል ህ መልኩ ፡ ቁመቱ ፡ በጠቅላላው ሁለ ንተናው አሁን እዚህ የምናየውን ይህ ህን ሰው በሕልሜ አየዋለሁ ። « ሳትዘ ገይ ፡ ውለህ - ሳታድር ተነስ ፡ ባሕሩን ቆርጠህ ተሻገር ፡ ሠራዊትህን መርቶ ከፊትህ ያለውን የፋርስን መንግሥት ግዛት በእጅህ እሰጥሃለሁ ፡ « ይለኛል ይህ ሰው ። ነገሩ እስከዚህ ድረስ ነው ። እንግዲህ ያለፈውንም ሆነ ወደፊት የ ሚጠብቀኝን ድል የምጎናጸፈው በእግ



www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ኃይል መሆኑን በእርግጥ አመንኩ ብሎ ከነገረው በኋላ ከሊቀ ካሕናቱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ካህናቱ ሕዝቡ አጅበዋቸው ወደ ከተማይቱ በደስታ ገባ ። ወደ ቤተ መቅደስም ወጥቶ በሊቀ ካህናቱ አማካይነት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ ። ካሕናቱንም አከበራቸው ። ሊቀ ካህናቱም ከ 300 ዓመት በፊት ነቢዩ ዳንኤል ያየውን የራእይ መጽሐፍ አቅርቦ ከግሪክ ነገሥታት አንዱ ተነስቶ የፋርስን መንግሥት ግዛት ይወስዳል « ሲል የተናገረውን ትንቢት ገልጦ ባሳየው ጊዜ ያ ሰው እኔ ነኝ ብሎ ስላመነ ደስታው እጥፍ - ድርብ ሆነ ። በማግሥቱም ካሕናቱን ጠርቶ ምን እንዲያደርግላቸው እንደሚፈልጉ በጠየቀቻው ጊዜ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣላቸውን የአባቶቻቸውን ሃይማኖት ሕግና ሥርዓት በነፃነት ለማክበር እንዲችሉ በየሰባተኛው ዓመትም ከግብር ነፃ እንዲሆኑ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀውት ይህንኑ ፈቅዶላቸዋል ።

ስለ ታላቁ እስክንድር አነሳስና ስለ ወራሾች ከ300 ዓመት በፊት የተነገረው ትንቢት በትክክል ተፈጽሞ መገኘቱና ትር ጓሜውም ዳን . ም ፡8 ከቁጥር 1 - 27 ይገኛል ።

ንቢዩ ዳንኤል ከክርስቶስ ልደት በፊት 700 ዓመት ላይ ተነስቶ የተናገረው ትንቢት እጅግ ጥልቅና ምጡቅ ምስጢርነት ያለው ስለሆነ በየዘመኑ የተነሱ የቤተ ክርስቲያን መምህራን በመመርመርና ከየዘመናቱ ታሪክ ጋር እያገናዘቡ በማጥናት ብዙ መጻሕፍት አቆይተውናል ።

እጅጉ ረታ

## ማ ሳ ሰ ቢ ያ ፤

1. ከመስከረም ወር 1974 ዓ/ም ጀምሮ ማንኛውም በጎ አድራጊ ድርጅት፣ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለድርጅታችን አስፈላጊውን ወጪ ይኸውም በወር ብር 24.00 ሂሣብ ከፍሎ በስሙ አንድ እጓለ ማውታ ወይም ችግረኛ ሕፃን ለማሳደግ ፈቃደኛ ከሆነ ጥያቄውን በመልእክት ሣጥን ቍጥር 30269

በስልክ ቍጥር 124261 አዲስ አበባ ቢያቀርብ የምንቀበል መሆኑን

እናሳስባለን ።

የሕፃናት አስተዳደር ጉባኤ ።



## ቤተሰብእ ....

ከገጽ ፩ የዞረ

ልዩ አገልግሎት በመስጠት ለ12 ዓመት ያህል አገለገልሁ፡ብለዋል ።እንደ፡ገናም ደብረ ብርሃን ውስጥ ያለው ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ከገደል አጠገብ በመሆኑ ሕዝብ በዓመት እንኳ አይሳለመውም ነበርና ያንን አስተካክለው ለማሰራት ሕዝቡን በማስተባበርና ድርሻቸውንም በማዋጣት ስለአሰሩት ባካባቢው ያለው ሕዝብ ያለ ድካም እየሄደ በየዕለቱ ጸሎቱን ያደርስበታል ። እንደ ገናም ለጥቂት ጊዜ የተውትን ሥራቸውን በመቀጠል በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ገብተው በዳግማዊ ምኒልክ ት ቤት ውስጥ ለ18 ዓመት ያህል በመምህርነት ካገለገሉ በኋላ አሁን በጡረታ ክልል ላይ እንዳሉ ነግረውናል ። በዚህ ጊዜያቸው ምን ምን እንደሚያደርጉ ለጠየቅናቸው ሲመልሱ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማንበብ በተለይም የቅዱስ ዑራኤልን ድርሳን እስካሁን የተረጐመው ስላልነበረ ግእዙን ወደ አማርኛ ተርጉመው ለቅዱስ ፓትርያርኩ ቀርቦ ባሳን ሱር ላይ ይገኛል ።

አለቃ ሲራክ ይህንን ሁሉ አገልግሎት በተለያዩ ቦታዎች ሲያካሂዱ በሕገ ጋብቻ መወሰናቸው ምንም እክል አልፈጠረባቸውም ። አለቃ ሲራክ አምስት ልጆች እንደወለዱ ባለቤታቸው በሞት ስለ ተለዩአቸው እነዚሁኑ ልጆች በምግባርና በሃይማኖት ኮትኩተው በትምህርት አንጸው በማሳደጋቸው ሁሉም ትምህርታቸውን ጨርሰው አገራቸውንና እራሳቸውን በሥራ እየረዱ እንዲኖሩ ከማድረጋቸውም ሌላ ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋው ደሙ እንዲፈጽሙ አብቅተዋቸዋል ። እነርሱም የራሳቸውን

አሌቃ ሲራክ ከአምስቱ ልጆቻቸው ጋር



ወ/ሮ ጽጌ ሲራክ



አለቃ ሲራክ ፈቃዴ ሥላሴ



ወ/ሮ የትም ወርቅ ሲራክ



አቶ ኃይለ መለኮት ሲራክ



ወ/ት ፀሐይ ሲራክ



አቶ ኤልያስ ሲራክ



www.ethiopianorthodox.org

ቤተሰብ መሥርተው ይገኛሉ ። አለቃ ሲራክም ሚስታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩአቸው በኋላ የቅስናን ማዕረግ ተቀብለው በደብረሊባኖስ ገዳም መን ኩሰው በአሁኑ ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር የሚገኙ የ67 ዓመትአዛውንት ናቸው ። የአለቃ ሲራክም አርአያነት ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፈው መልእክት ብዙ ነው ። ትምህርታቸውን አጠናቀው መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ጠብቀው



አለቃ ሲራክ በምንኩስናቸው

ባሉበት ሕይወት በመጽናት በቤተሰብ ኃላፊ መሆናቸውና በተለያዩ ቦታዎች ከሚሰጡት አገልግሎት እንቅፋት ሳይ ሆንባቸው በሁሉም በኩል በኑሮአቸው ሊያደርጉት የሚገባቸውን በመልካም ሁኔታ ፈጽመውታል ።

እንግዲህ ከቤተሰብም ሃላፊዎች የሚጠበቀው መልካም የአኗኗር ውጤት ይህ ነው ። ምሳሌነቱንም ለሚከተል ከትርፍ በቀር የሚያጎድለው የለም ።

## ደብዳቤዎች ...

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ተቀል የጐደለው ሞኝነት ነው መፍት ሔ ሀብት እግዚአብሔር በግንባርህ ወ ዝ ብላ ባለው መሠረት ሳይሰንፉ ጠን ክሮ መሥራት ነው ፣ በዚህ በማታለል ተግባር ለሚኖሩ ሰዎች የምንሰጣቸው ምክር ወደፊት ከማታለል ተግባራ ቸው ተወግደው ወጥተው ወርደው ፣ የጉልበታቸውን አላባ እንዲመገቡ ነው ።

በእርግጥ የሚያውቁት ጥበብ ካለ ከ ላይ እንደተጠቀሰው ያነኑ ያላቸውን ጥበብ ለጤና ጥበቃ በማቅረብና በመወ ያየት ለሕዝብ ጥቅም ሊያውሉት ይች ላሉ የሰው ገንዘብ በማታለል መን ጠቅ ተገቢ አይደለምና ሴቶችም ቢሆኑ ወደ አታላዮች አዘወትረው መሄዳቸ ውን ትተው እየሠሩ መኖር አለባቸው መፍትሔ ሀብት ሥራ ነውና ።

## ቅዱስ ማቴዎስ .....

ከገጽ ፫ የዞረ

ሐዋርያ ማቴዎስ በመጨረሻ አንትሮ ፋጊ ወደሚባለው ሀገረ በላዕተ ሰብእ ሄደ ጥቅምት ፲፪ ቀን በመጀመሪያው ምእት ዓመት በሰማዕትነት ሞቷል አን ትሮፋጊ በዛሬው ዓለም የትኛው እን ደሆነ አይታወቅም ።

ማቴዎስ ከቀራጭነት ወደ ወንጌል መልእክተኛነት በመመለሱና ቅዱስ ወ ንጌልን በመጻፉ ፣ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ም በሰማዕትነት በመሞቱ ፣ ለክርስቲያ ኖች ሁሉ ታላቅ ምሳሌነት ያለው መም ህር ነው ።

እነሆ ቀራጩን ወንጌላዊ ያደረገው ወንበዴውን በቅፅበት (በሰከንድ) የመ ረጠው ክርስቶስ በማንኛውም ኃጢአት ውስጥ ያሉትን ሁሉ በረድኤቱ ሊያቀር ባቸው የተስፋ ወራሾችም ሊያደርጋ ቸው ስለሚችል እንዲህ ሲል ይጠራቸ ዋል "ኑ ተከተሉኝ"

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org